ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 061 ኅዳር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# "አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣናው ወጥ የአፍሪካ የገበያ ሥርዓት ለመገንባት የሚያግዝ ነው"

- ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ

ሞገስ ጸጋዬ


ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ወጥና ጠንካራ የሆነ የአፍሪካ የገበያ ሥርዓት ለመገንባት አጋዥ መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሴክሬታሪያት 15ኛው የንግድ ሚኒስትሮች ካውንስል ጉባኤ ትናንት በአዲስ አበባ አፍሪካ ህብረት የስብሰባ አዳራሽ ተካሂዷል።

ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ በአፍሪካ የታሰበውን ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት ወጥ የገበያ ሥርዓት ሊኖር ይገባል። ከዚህ አኳያም ነጻ የንግድ ቀጣናው በየሀገራቱ የተበጣጠሰውን የገበያ ሥርዓት በማስቀረት ወጥ ወደሆነና ጠንካራ የአፍሪካ የገበያ ሥርዓት ለመገንባት ይረዳል። እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ የአፍሪካን ንግድ ያሳድጋል።

ነጻ የንግድ ቀጣናው የጋራ የሆኑት የአፍሪካን ግቦች ለማሳካት ትልቅ መንገድ እንደሚሆን ጠቁመው፤ ዘላቂ እድገት ለማረጋገጥ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣናን በፍጥነት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ

"አህጉራዊ ነፃ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል












ፎቶ፡ ገበየ ገብሬ

ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ

## የሀገርን ሉዓላዊነትና ሰላም የሚያስከብር የሠራዊት ግንባታ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

ዘላለም ግዛው

ሁርሶ፡- የሀገርን ሉዓላዊነትና ሰላም የሚያስከብር ጠንካራ የሠራዊት ግንባታ ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ ገለጹ።

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የትምህርት እና ስልጠና ዋና መምሪያ የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ እና የሁርሶ የእጩ መኮንን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የ25ኛ ዙር

የሀገርን ሉዓላዊነትና... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## ትኩረት የሚሻው የተማሪዎች ሥነ ምግባር

ማህሌት ብዙነህ

መምህርት አመለወርቅ ገዛኸኝ በመምህርነት ሙያ ለስምንት ዓመታት አገልግለዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት በተማሪዎች ሥነ ምግባር ዙሪያ ብዙ ነገር ታዝበዋል፤ተመልክተዋል፡፡

የነገ ሀገር ተረካቢዎችን በሥነምግባር የማፍራት ኃላፊነት ባለባቸው በትምህርት ተቋማት ውስጥ መልካም ሥነምግባር ያላቸው ተማሪዎች እንዳሉ ሁሉ ሲጋራ፣ጫት እና የመሳሰሉ አደንዛዥ እጾች ሱሰኛ የሆኑ፣ አልባሌ ቦታ የሚውሉ፣ ካለበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት የሚቀሩ፣ ኩረጃን ልምድ ያደረጉ እና የቡድን ጸብ ላይ የሚሰማሩ ተማሪዎችን ማየት የተለመደ ነው ይላሉ መምህሯ፡፡



ለራሳቸው እና ለቤተሰቦቻቸው የሚያስቡ ተማሪዎች እንዳሉ ሁሉ ሥነምግባር የጎደላቸው ተማሪዎች አሉ የሚሉት ለስምንት ዓመታት ያህል በመምህርነት ያሳለፉት መምህርት አመለወርቅ ገዛኸኝ፤ እሳቸው በሚያስተምሩበት ሆነ በሌላ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ከቤታቸው ሲወጡ የለበሱትን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) መንገድ ላይ በሌላ ልብስ በመቀየር ትምህርታቸውን በመከታተል ፋንታ መገኘት በሌለባቸው አልባሌ ቦታ ሲያሳልፉ እንደሚታዩ ይገልጻሉ፡፡

ለዚህ ሥነምግባር የጎደለው ተግባርም የጓደኛ ጫና እና የቤተሰብ አስተዳደግ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን አንስተው፤ የወላጆችና የመምህራን ያልተገባ የቁጥጥር ዘይቤም በተማሪዎች ዘንድ አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ይናገራሉ፡፡

የልጆችን በመልካም ስብእና ለማነጽ ወላጆችና መምህራን ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው የሚናገሩት መምህሯ፤ ቤተሰብ ልጆቹን አቅርቦ ማናገር እና የእለት እለት እንቅስቃሴያቸውን መከታተል እንዲሁም መምህራን ለተማሪዎቻቸው አርአያ በመሆንና ቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በሥነ ምግባር የታነጹ ሀገር ተረካቢዎችን ማፍራት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

ተማሪዎችን በሥነ ምግባር ለማነጽ ስድቦችንና አካላዊ ቅጣትን መጠቀም ተማሪዎቹን ለንዴት፣ እልኸኝነትና ስሜታዊነት

ትኩረት የሚሻው... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






## አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለኢኮኖሚው እድገት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል

ገጽ 5



ዜና

# የአምራች ኢንዱስትሪው በትራንስፖርት ዘርፍ ያለውን ውስንነት መቅረፍ የሚችል አቅም ማዳበር ይኖርበታል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪው በትራንስፖርት ዘርፍ ያለው ውስንነቶች በቀላሉ መቅረፍ የሚችል አቅም ማዳበር እንደሚኖርበት የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያበቁ ተሽከርካሪዎች መልሶ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እና የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ ያለመ የባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ ትናንት ተካሂዷል፡፡

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ(ዶ/ር) በዕለቱ እንደገለጹት፤ የትራንስፖርት ዘርፍ ለማሳደግ እንዲሁም አገልግሎቱን ለማሻሻል የአምራች ኢንዱስትሪው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ይህን ሚናውን ለመወጣትም አቅሙን ማጎልበት ይጠበቅበታል፡፡

በኢትዮጵያ ተሽከርካሪዎች፣የተሽከርካሪ ቦዲዎችንና መለዋወጫዎች በሀገር ውስጥ በብዛት የማይመረቱ በመሆኑ በትራንስፖርቱ ዘርፍ በርካታ ክፍተቶች እንዲኖር አድርጎታል ያሉት ሚኒስትሩ፤ አሁን ላይ የተሽከርካሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተኬደ ያለበት ርቀት ችግሩን በቀላሉ መፍታት የሚችል ነው ብለዋል፡፡

ከውጭ የሚገባ ምርት በሀገር ውስጥ መተካት ለኢኮኖሚያዊ እድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑን ገልጸው፤በርካታ ሀገራት በሚፈለገው ፍጥነት ማደግ ያልቻሉት የሀገር ውስጥ አቅም ማዳበር ስላልቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡



**አለሙ ስሜ(ዶ/ር)**

ኢትዮጵያም ይህ እጣ ፈንታ እንዳይገጥማት ከወዲሁ የሀገር ውስጥ አቅም ማሳደግ እንዳለባት አመልክተው፤የመንግሥት ተቋማት በሀገር ውስጥ የሚመረት ምርት እያለ ከውጭ እንዳይገዙ ተብሎ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዘርፉ እውቀቱና አቅሙ ያላቸው ተቋማትን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባም ነው ሚኒስትሩ የጠቆሙት፡፡

እንደ አለሙ (ዶ/ር) ገልጻ፤ የሀገር ውስጥ ምርት ማሳደግ የመለዋወጫ ችግር ለመቅረፍ እንዲሁም ብልሽት ሲገጥም የባለሙያ እጥረት እንዳያጋጥም የሚያደርግ ነው፡፡

በቅርቡ የተጀመረው ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄም በርካታ ሀብት ከማፍራት በተጨማሪ በቢሊዮን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት አስችሏል፡፡ በቀጣይም በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች ድጋፍና ክትትል ሥራው ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ትራንስፖርት አሰሪዎች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኔ ዘሩ በበኩላቸው፤ ፌዴሬሽኑ በትራንስፖርት ዘርፍ የተሻለ ውጤት እንዲገኝና ኢትዮጵያ ታምርትን በማጠናከር የሀብት ብክነት እንዳይከሰት አገልግሎት ጨርሰው የቆሙ ተሽከርካሪዎችን እያደሰ ዳግም ወደ አገልግሎት እያስገባ ይገኛል ብለዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ከ500 በላይ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ዳግም ወደ ስራ ለመመለስ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ብርሃኔ፤ይህም የውጭ ምንዛሬ ለማዳንና ኢኮኖሚውን ለመደገፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አብራርተዋል፡፡

ዳግም ወደ አገልግሎት የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም ከጥራት አኳያ ምን ያህል አስተማማኝ ናቸው ለሚለው ከአምራቾቹ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተውጣጡ አካላት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንደሚሰራ አስረድተዋል፡፡

በውይይት መድረኩ የተለያዩ የመኪናና የመኪና ቦዲ አምራቾች፣ የነዳጅ መኪናዎችን ወደ ኤሌክትሪክ የሚቀይሩ ድርጅቶች፣ የታክሲ ማህበራት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ሚኒስቴር ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

# የአቪዬሽን ዘርፉ ለግል አልሚዎች ክፍት መደረጉ ሰፊ የሥራ እድልን ይፈጥራል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ ፡- የአቪዬሽን ዘርፉ ለግል አልሚዎች ክፍት መደረጉ ለወጣቶች ሰፊ የሥራ እድል እንደሚፈጥር የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ።

ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በድህረ-ምረቃ ፣ በቅድመ-ምረቃ፣ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በሰርተፊኬት ፕሮግራሞች ያሰለጠናቸውን 974 ተማሪዎች ትናንት አስመርቋል።

በወቅቱ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ተሻለ በሬቻ እንደገለጹት፤ የአቪዬሽን ኢኮኖሚው ለግሉ ዘርፍ ክፍት መደረጉ ወጣቶች የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ አይነተኛ ሚና አለው።

መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለግሉ ዘርፍ ክፍት በማድረጉ በአቪዬሽን መስክ በርካታ ተቋማት ተሰማርተው ኢኮኖሚውን ከማንቀሳቀስ ባለፈ የሥራ ዕድል እየፈጠሩ መሆኑን አንስተዋል።

ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅም በገበያው ላይ የሚፈለጉ የትምህርት መስኮችን በማስተማር በተለይም በአቬሽን ዘርፉ ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በመቅረፍ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዕውቀት በተግባር ካልተደገፈ ውጤታማ ስለማይሆን ወጣቶች አጫጭር ስልጠናዎችን በመውሰድ ለዓለም አቀፍ የሥራ እድሎች ያላቸውን ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ እንደሚገባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

መመረቅ በራሱ ግብ አይደለም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ምሩቃኑ ለቀጣይ እራሳቸውን ብሎም ሀገርን ለመለወጥ መዘጋጀት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በርካታ የሥራ እድሎች ማመቻቸቱን ገልጸው፤ ከሀገር ውጭ መሥራት ለሚፈልጉ የውጭ የሥራ ስምሪት መኖሩን ፣ በግል ለሚሰሩ ደግሞ የቦታ፣ የብድርና መሰል እድሎች መመቻቸታቸውን አመላክተዋል።

የናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚና መስራች የሆኑት ካፒቴን አበራ ለሚ፤ ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በቅርቡ ዩኒቨርሲቲ የመሆን ዓላማ ሰንቆ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።



ኮሌጁ በተሟላ ግብዓትና የስልጠና ዘርፎች ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

የናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገዛኸኝ ብሩ በበኩላቸው፤ በአቪዬሽን፣ በሆቴልና በቱሪዝም መስኮች እያደገ የመጣውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ከማሟላት አኳያ ብቁ ሙያተኞችን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት መቀጠሉን ተናግረዋል።

ከኮሌጁ ሰልጥነው የሚወጡ ተማሪዎች በተመረቁበት የትምህርት ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ስልጠናዎች ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

ኮሌጁ ከሲቪል አቬሽን ባለስልጣን እውቅና ባገኘበት በአውሮፕላን ጥገና ቴክኒሽያንነት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን የጀመረ ብቸኛ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መሆኑን ተናግረዋል።

ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ የናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ አባል እና የናሽናል አየር መንገድ እህት ኩባንያ ነው።

በወዳጅነት አደባባይ በተካሄደው የምርቃት ሥነ ሥርዓት ላይ የክብር እንግዶች፣ የኮሌጁ ከፍተኛ አመራሮች፣ ተመራቂ ተማሪዎችና የተመራቂ ቤተሰቦችን ጨምሮ በርካታ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# በመዲናዋ አረንጓዴ ስፍራዎችን ለመንከባከብ አራት ሺህ 600 ልማት ሠራዊት ማሰማራት ተችሏል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አረንጓዴ ስፍራዎች በዘላቂነት ለመንከባከብ ከአራት ሺህ 600 በላይ የአረንጓዴ ልማት ሠራዊት ወደ ስራ ማሰማራት መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ እየተሰሩ ያሉ የአረንጓዴ መሰረተ ልማትና የኮሪደር ልማት ስራዎችን በዘላቂነት ለማስቀጠልና የለሙ ቦታዎችን ባለቤት ለመስጠት ያለመ የንቅናቄ መርሀ ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ይመኙሻል ታደሰ በወቅቱ እንደገለጹት፤የኮሪደር ልማት ዘርፍ አንዱ በሆነው የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስራ ከተማዋን በተፈጥሮ የበለጸገችና ለመኖር ተስማሚ የአፍሪካ ግንባር ቀደም ከተማ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ አረንጓዴ ስፍራዎች በዘላቂነት ለመንከባከብም ከአራት ሺህ 600 በላይ የአረንጓዴ ልማት ሠራዊት በዘርፉ በማሰልጠን የስራ ስምሪት መስጠት ተችሏል፡፡

የከተማዋን አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ደረጃዋን የሚመጥን ዘመን ተሻጋሪ ከተማ ለመገንባት በሚ ያስችለው የኮሪደር የአረንጓዴ ልማት ብዙ በተጨባጭ የሚታዩና የሚቆጠሩ ድሎች መመዝገቡን ገልጸው፤እነዚህን የአረንጓዴ ስፍራዎች ውበታቸው እንደተጠበቀ ለማስቀጠል ከአራት ሺህ 600 በላይ የአረንጓዴ ልማት ሠራዊት በዘርፉ በማሰልጠን የስራ ስምሪት መደረጉን ተናግረዋል፡፡

የከተማውን እድገትና መስፋፋት ተከትሎ በሚሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች ከ603 ሄክታር መሬት በላይ አረንጓዴ ቦታዎችን ማልማት መቻሉን አመልክተው፤ 60 ሄክታር መሬት በኮሪደር አረንጓዴ ልማት የተሸፈነ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከ70 በላይ የሚሆኑ የህዝብ መናፈሻዎች እና 38 የውሀ አካላት መልማታቸውን ገልጸዋል፡፡

ኮሪደር አረንጓዴ ልማትና ባለፉት አምስት ዓመታት በከተማዋ በተከናወኑ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ስራዎች ተከትሎ የአዲስ አበባ አረንጓዴ ሽፋን ከ2 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 20 በመቶ ከፍ ማድረግ እንደተቻለ አስታውቀዋል፡፡

ለዓይን የማይመቹ አካባቢዎችና ለአፍንጫ የሚሰነፍጡ ወንዞች የከተማዋ መለያ እስኪመስል ድረስ የከተማዋን ገጽታ አደብዝዘው እንደነበር አንስተው፤ በተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራም በአረንጓዴ በተዋቡ ሰፈሮች ተቀይረዋል ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ይመኙሻል እንደገለጹት፤ አረንጓዴ ከተማ ግንባታ ሲባል በአካልና በአዕምሮ የዳበረ የነገዋን ኢትዮጵያ ተረካቢ ጤናማ ትውልድ መፍጠር ነው፡፡ ለዚህም በሁሉም መዳረሻዎች ዘመኑን የዋጁ የተለያዩ የህጻናት አዕምሮ ማጎልበቻና አረንጓዴ ቦታዎች ተገንብተዋል፡፡እነዚህ የለሙ አረንጓዴ ቦታዎች በዘላቂነት በእንክብካቤ ለማስቀጠልም ከ4 ሺህ 600 በላይ የአረንጓዴ ልማት ሠራዊት በዘርፉ በማሰልጠን የስራ ስምሪት መስጠት ተችሏል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ለከተማዋ ሌላኛው የቱሪዝም የገቢ ምንጭ መሆን የቻሉ የህዝብ መዝናኛዎችን ገንብቶ ለህዝብ አገልግሎት ክፍት የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘርፉም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን የስራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ከተማዋን አረንጓዴ ከተማ ገንብቶ ለትውልድ ለማስተላለፍ በሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አስታውቀው፤ ሁሉም አካል በኮሪደር ልማቱ ውጤቶችን በዘላቂነት ለማስቀጠል ኃላፊነት መወጣት እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡፡

በህዝብ ንቅናቄ መድረኩ ከ11ዱም ክፍለ ከተሞች ለተመረጡ ተጽእኖ ፈጣሪና ታዋቂ ግለሰቦችም የአረንጓዴ ልማት አምባሳደርነት ተሰጥቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሃይማኖት ተቋማት ለሠላም መስፈን ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊሠሩ ይገባል !

ሠላምን በማስፈን እና በማጽናት ሂደት ውስጥ  የሃይማኖት ተቋማት የማይተካ አስተዋፅዖ አላቸው። ትውልዶችን በሞራልና በሥነ ምግባር በማነጽ ለራሳቸው፣ ለማኅበረሰባቸው እና ለሀገራቸው ሠላም አቅም በመሆን ሊያገለግሉ እንደሚችሉ በእጅጉ ይታመናል። ለዘመናት ሲሆን የነበረው እውነታም ይህንኑ የሚያጸና ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የየትኛውም ሃይማኖት አስተምሕሮ ሠላምን መሠረት ያደረገ እና የሚያጸና ነው። ግለሰቦች ከራሳቸውና ከማኅበረሰባቸው ጋር ያላቸውን የዕለት ተዕለት መስተጋብር ሠላማዊ እንዲሆን የሚያስችሉ ማኅበራዊ እሴቶችን ማጎልበት፣ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር የሁሉም ሃይማኖቶች የጋራ መገለጫ መሆኑም ይታወቃል።

የመቻቻልና አብሮ የመኖር እሴቶችን እንዲሁም ማኅበራዊ ትስስሮችን በማጠናከር በሠላም ግንባታውም ሆነ፣ በዜጎች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ መከፋፈሎችን በማስወገድና ጠንካራ ሀገራዊ አንድነት በማምጣት፣ ሀገረ መንግሥትን  በማጽናት ሂደትም የሃይማኖት ተቋማት ተልዕኮ ከፍ ይላል።

ይህንን እውነታ ታሳቢ በማድረግም የሃይማኖት ተቋማት በየትኛውም ጊዜ እና ሁኔታ ውስጥ ሆነው ስለሠላም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማሰማታቸው ተለምዷል። ችግሮችን ወይም አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ በውይይት እና  በይቅርታ የመፍታት መንገድን በማስተማር በማኅበረሰብ ውስጥ ሠላም እንዲጸና አብዝተው ይተጋሉ።

ይህ ትጋታቸው በቀደሙት ዘመናትም ሆነ ዛሬ በዓለም አቀፍ፤ በሀገር አቀፍ እንዲሁም በማኅበረሰብ ደረጃ የሠላም እሴቶች ጸንተው ለመቆማቸው በዋነኛነት ይጠቀሳሉ። በቀጣይ ለሚኖረውም የሰው ልጅ ሠላም ትልቅ አቅም ሆነው እንደሚያገለግሉም ይታመናል ።

በተለይም ባለንበት ዘመን የጽንፈኝነትና የመከፋፈል ሀሳብ አብሮ በመኖር ላይ የተደቀነ ዓለም አቀፍ ስጋት ወይም አደጋ እየሆነ በመጣበት ሁኔታ፣ የሃይማኖት ተቋማት የጽንፈኝነትና የመከፋፈል ሀሳብን ለመቋቋም ትልቅ ጉልበት  እንደሚሆኑ፤ ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት እንደሚኖራቸው ይገመታል።

በሃይማኖቶች መካካል መቻቻልን ከማጎልበት ጀምሮ፣ የሠላም እሴቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማጠናከር፣ ዓለም አሁን ላይ እያጋጠማት ካለው የሠላም እጦት ወጥታ የተረጋጋች እንድትሆን ተቋማቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ።

ራስ ወዳድነት እና ኢ-ፍትሐዊነት፤ ጽንፈኝነትና አሸባሪነት ለዓለም ሠላም እና ሁለንተናዊ እድገት ዋነኛ ፈተና እየሆኑ ባሉበት በአሁኑ ወቅት፣ የሃይማኖት ተቋማት ራሳቸውን ከችግሩ አርቀው የመፍትሔው አካል መሆን፤ ችግሮች በሠላማዊ መንገድ በውይይት እና በድርድር የሚፈቱባቸውን መንገዶች ማመቻቸትና ማመላከት በሚኖርባቸው ወሳኝ ወቅት ላይ እንደሚገኙ ተገንዝበው አጥብቀው ሊሠሩም ይገባል።

ለሠላም እና ለሠላም እሴቶች የተገዛ ትውልድ በመፍጠር ሂደት ውስጥ ያላቸውን ትልቅ ሚና በአግባቡ መወጣት፣ የሕዝቦችን በሠላም አብሮ የመኖርና የመከባበር እሴቶችን ይበልጥ አጠናክሮ ማስቀጠል፣ እሴቶቹ ተጠብቀው ለትውልዶች  እንዲተላለፉ ያላቸውን የማይተካ ሚና መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

የሁሉም ነገር መነሻና መድረሻ ሠላም በመሆኑ ሠላም በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በሀገር አቀፍ፣ ከዛም ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሰፍን ለማድረግም የሃይማኖት ተቋማት ለዚህ የሚሆን በቂ ዝግጁነት በመፍጠር ተጨባጭ ተግባር ማከናወን አለባቸው። ከሠላም ጋር ካላቸው የጠበቀ ቁርኝት አኳያም፤ በሃይማኖታዊ አስተምሕሮታቸው ለሠላም ቀጣይነት ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ፣ ይህንን የሚሸከም ተቋማዊ  ምሕዳር ሊፈጥሩም ይገባል።

ለሁለንተናዊ ዓለም አቀፋዊ ሠላም መስፈን፤ የየትኛውም ሃይማኖት ተቋም ተከታይ ምዕመን፣ ራሱን የሠላም ሐዋርያ አድርጎ መንቀሳቀስ የሚያስችለውን ግለሰባዊ ማንነት መገንባት የሚያስችል ተቋማዊ ዝግጁነት በመፍጠር  በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ  የሃይማኖት ተቋማቱ አሁናዊ  ዋንኛ ተልዕኮ መሆንም ይኖርበታል።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የፍራንኮ ቫሉታው ውጤት ፍተሻና የውሳኔው ተገቢነት

**ታምራት ተስፋዬ**

ፍራንኮ ቫሉታ /Franco- Valuta/ ሕጋዊ ከሆነ ምንጭ የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ሲሆን የባንክ ቤት ፈቃድ (Bank Permit) ሳያስፈልገው ከውጪ ሀገር ዕቃ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድ ነው። የፍራንኮ ቫሉታ መብት ያላቸው አስመጪዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቧቸው ምርቶች የውጪ ምንዛሪን በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ የወጡ እና በንግድ ባንኮች የሚተገበሩ ጥብቅ መመሪያዎችን የማለፍ ግዴታ የለባቸውም። ይህም ማለት የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት የባንክ ቤቶች ፍቃድ ሳያስፈልገው በፍራንኮ ቫሉታ የሚገቡ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት መብት ያገኛል ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ያለምንም የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ምርቶችን ማስገባት በተለይ የገቢ ንግድን ለማሻሻል እና ለማረጋጋት በተለያዩ ጊዜያት ሲፈቀድ ተመልሶም ሲከለከል ቆይቷል። የተለያዩ የምጣኔ ሃብት ምሑራን እንደሚያስረዱት ከሆነም፣ ፍራንኮ ቫሉታ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በተለይ የሀገር ኢኮኖሚ ሲንገጫገጭና ግሽበት ሲከሰት ዋጋን ከማረጋጋት አንፃር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው።

ፍራንኮ ቫሉታ በተለይም የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስና የምርት አቅርቦትን ለመጨመር ይረዳል። የሀገር ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦትም አለመመጣጠን በማስተካከል፤ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትና የምርት እጥረትን ለመቅረፍ ጊዜያዊም ቢሆን ጥሩ መፍትሔ ተደርጎ የሚታይ ነው።

የገንዘብ ሚኒስቴር ከዓመት በፊት በተለይ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን ያለውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት እንዲቻልና ፍራንኮ ቫሉታን መፍቀዱ የሚታወስ ነው። መንግሥት በከፍተኛ ወጪ በመግዛት በዝቅተኛ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ከሚያቀርባቸው መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች በተጨማሪ በሌሎች አካላት የሚገባውን በማከል አቅርቦቱ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምር ዘንድ ያለውጭ ምንዛሪ ሸቀጦችን የማስገባት አሠራር መፈቀዱ በሀገሪቱ የሚስተዋለው የዋጋ ንረት ከዚህም በከፋ መልኩ እንዳይሰቀል ትልቅ አቅም መፍጠሩም የሚካድ አይደለም። በትግበራ ሂደትም መንግሥት ማግኘት የነበረበትን ከፍተኛ ገቢ ማጣት ግድ ብሎታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከዓመት በፊት ለምክር ቤት በሰጡት ማብራሪያ ካነሷቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከልም ፍራንኮ ቫሉታ ጉዳይ አንደኛው ነው። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግሥት እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እንዲቻል በወሰነው ፍራንኮ ቫሉታ 10 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት እየቻለ ማጣቱን መጠቆማቸውም የሚታወስ ነው።

በእርግጥም ፍራንኮ ቫሉታ አማራጭ መፍትሔ ከመሆኑ ባሻገር የራሱ የሆኑ ፈተናዎችን ይዞ ይመጣል። የፍራንኮ ቫሉታ ተግባራዊ በሆነባቸው ሀገራት ሆነ የምጣኔ ሃብት ምሑራኑ ሲያስረዱ እንደሚታየው፣ እንደሚደመጠው፣ የፍራንኮ ቫሉታ ተግባር ከፍተኛ ጥንቃቄን የግድ የሚል ነው። የፈቃዱን ዓላማ ለማሳካት ሳይሆን የራሳቸውን ጥቅም ለማዳበር የሚፈልጉ ግለሰቦች ያላግባብ እንዳይጠቀሙበት ሂደቱ በጥብቅ ሥነ ምግባር ሊመራ ይገባል።

ከሁሉ በላይ ጠንካራ ቁጥጥር እጅግ ወሳኝ ነው። በትግበራ ወቅት ከቁጥጥር ጋር በተያያዘ በሚስተዋሉ ድክመቶችና በሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ተግባራት ሀገር የሚያስፈልጋትና ወደ ሀገር የሚገባው የተለያየ ሊሆን ይችላል። ተጠቃሚዎቹ እንጂ አገር የምትፈልገው ላይገባም የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ ነው።

ተጠቃሚዎቹ ትርፍን ብቻ ታሳቢ በማድረግ የሚፈልጉትን ምርት ወደ ሀገር ውስጥ አስገቡ ማለት ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሀገርን ኢኮኖሚ ይጎዳል። ገበያ ላይ ያሉ በተለይ በሀገር ውስጥ መመረት የሚችሉት ሳይቀር በዝቅተኛ ዋጋ የሚገቡ ከሆነ ደግሞ የአገር ውስጥ አምራቾችን ያደቃል። በማደግ ላይ ያሉ ፋብሪካዎችን ያቀጭጫል።

ፍንራኮ ቫሉታ፣ በተለይ በተለይ የጥቁር ገበያን በማስፋፋት ረገድ ከባድ ተፅዕኖ እንዳለውም እሙን ነው። ከሁሉ በላይ በወንጀል የተገኘ ገንዘብንም በእግረ መንገድ ሕጋዊ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል። አሠራሩ ጥንቃቄ ካልተደረገበት ግለሰቦች በትይዩ ገበያ ገዝተው ያስቀመጡትን ወይም ያጠራቀሙትን የውጭ ምንዛሪ የሚያጥቡበት ወይም ሕጋዊ የሚያደርጉበት ሁኔታን ሊያመቻች ይችላል።

መሰል ችግሮችን ለመሻገር ከትርፉም በላይ ኪሳራን ለመራቅ በፈቃዱ ምን ውጤቱ ታይቷል? ገበያውስ ተረጋግቷል? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ በየጊዜው መቃኘት የግድ ይላል። አፈፃፀሙንም በየጊዜው በመከታተል የተፈለገውን ውጤት አምጥቷል፣ አላመጣም፣ የሚለውን መገምገም የግድ ነው። ከዚህ ባሻገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ምርቶች መንግሥት ፈቃድ የሰጣቸው ናቸው? አይደሉም የሚለውን መፈተሽም ተገቢ ነው።

ከዚህም ከፍ ሲል ውጤቱ እየታየ ማሻሻያዎች ካስፈለገ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል። ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከቀናት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው በሰጡት ማብራሪያ ላይ የፍራንኮ ቫሉታን አተገባበር መንግሥት እየፈተሸው መሆኑን አሳውቀው ነበር።

‹‹ባለፉት ጥቂት ወራት ከሪፎርሙ ጋር ተያይዞ ከወሰናቸው አብረው ከማይሄዱ ውሳኔዎች ውስጥ አንዱ ፍራንኮ ቫሉታ ነው። ያን የወሰንበት ምክንያት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩን። አንደኛው በውጭ ያለ ሀብት ከዚህ ቀደም የሸሸ ወደ ሀገር ውስጥ መምጣት የሚችል ከሆነ ዕድል ለመስጠት ሁለተኛ ባንኮቻችን አሁን በጀመርነው ኢኮኖሚክ ኦፐን አፕ በቂ ልምምድ እስኪያደርጉ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦች እንዳያንሱ እና የኑሮ ውድነትን እንዳያባብሱ ጉዳት ቢኖረውም ከፈት እናድርግ የሚል እሳቤ ነበረን። ያየነው ውጤት ከዚህ በላይ መሸከም ተገቢ እንዳልሆነ የሚያሳይ በመሆኑ በቅርቡ ፍራንኮ ቫሉታን በሚመለከት ማስተካከያ እንደሚደረግ ይጠበቃል›› ነው ያሉት።

ይህን ተከትሎም መንግሥት የፍራንኮ ቫሉታ ትግበራውን በመፈተሽ መሻሻል የሚገቡ ብሎም መለወጥ ያለባቸውን ጉዳዮች በመገምገም የለውጥ እርምጃን ተከትሏል። በተለይ ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ መግባታ የፍራንኮ ቫሉታውን አጠቃላይ መልክ የሚቀይር እንደመሆኑ ለውጥ ማድረግ የግድ ነው። በዚህ አግባብ የፍራንኮ ቫሉታው ውጤት ተፈትሾ የተላለፈው ውሳኔም ተገቢነት ያለው ነው።

መታወቅ ያለበት ወሳኝ እውነት ቢኖር  ፍራንኮ ቫሉታ በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ችግር እንዲፈታ እንጂ ለረጅም ጊዜ የሚሆን መፍትሔ አለመሆኑ፣ ጊዜያዊና ችግሮቹ ይበልጥ እንዳይባባሱ ማድረግን ታሳቢ ያደረገና ለአጭር ጊዜ የሚሆን ማስተንፈሻ መሆኑ ነው። በተለይ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት በአጭር ጊዜ እንጂ በዘለቄነት መፍትሔ የሚያመጣ አይደለም። መንግሥት የትግበራውን አጠቃላይ ውጤትን መዝኖ ሊስተካከል ይገባል ማለቱም ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው።

ይሁንና ከመሰል ውሳኔዎች ባሻገር በተለይ ከእለት እለት እየተባባሰ የመጣውን ዋጋ ግሽበት ፈር ለማስያዝ ዘላቂው መፍትሔ የሀገሪቱን መዋቅራዊ ኢኮኖሚ ዑደት ማስተካከል መሆኑን መገንዘብ ይገባል። በተለይ ፍላጎትና አቅርቦት ምጥጥን ልዩነቱን ለማስተካከል ሀገር ውስጥ በተሻለ ማምረት የሚቻልበትን መንገድ መቀየስና ለዚህ ተግባራዊነትም ሌት ተቀን መትጋት የግድ ይላል።

በተለይም ከሠላም እና ፀጥታ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ችግሮች ፈጣን እልባት መስጠት፣ ሎጂስቲክስና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ በቋሚነት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግና ከውስጥ ፍላጎት አልፎም የውጭ ምንዛሪ ማስገባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምርቶችን በስፋት በሀገር ውስጥ ማምረት ብሎም ለውጭ ገበያ ማቅረብ ታሳቢ ማድረግ ይገባል።

# አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለኢኮኖሚው እድገት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዳማ፡- አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

በአዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ዙሪያ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የገለጻና ውይይት መድረክ በአዳማ ከተማ ትናንት ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል።

አዲሱ ፖሊሲ የቀድሞ ፖሊሲ ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ሆኖም የቀድሞው ፖሊሲ የግብርና ምርቶችን አቅርቦትን ማሳደግና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ክፍተት ነበረበት ብለዋል።

የግብርናና ገጠር ልማት ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ፣ በሀገር ደረጃ እየተከናወኑ ያሉትን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ፖሊሲውን መከለስ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የአዲሱ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ፣ የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት በዋናነትም ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው አብራርተዋል።

ፖሊሲው ሀገሪቷ የምትከተለውን የብዝሃ-ዘርፍ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ለማሳካት የሚያግዝ ነውም ብለዋል።



ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር)

ፖሊሲውን የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራው በቀጣይ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች እስከ ዞን እና ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የሚደረግ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ በበኩላቸው፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየመራ ያለውን ግብርና በሚመጥን ፖሊሲ ፣ አደረጃጀትና አመራር መደገፍ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ እንደ ሀገር ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ታስቦ የሚሰራው ሥራ ስኬታማ አይሆንም ብለዋል።

አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ የተከለሰበት ዋነኛው ምክንያት አሁን ሀገሪቱ ካለችበት እድገት አንፃር በቂና አስቻይ ባለመሆኑ ነው ያሉት ሰብሳቢው፤ በዚህም ወቅቱን የሚመጥን ፖሊሲ ማፅደቅ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ገልጸዋል።

የውይይት መድረኩ ከግብርና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ጋር በመሆን የተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል።

# የሀገርን ሉዓላዊነትና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሰላም ኮርስ እና የወልወል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

የመርሃ ግብሩ የክብር እንግዳ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ እንደገለጹት፤ ወታደራዊ አመራሮች እና አሰልጣኞች ዘመኑ የሚጠይቀውን ወታደራዊ ብቃት፣ እውቀት እና ጥበብ ለማስተላለፍ የሚካሄደው የሠራዊት የአቅም ግንባታ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የሀገርን ሉዓላዊነትና ሰላም ለማጽናት ጠንካራ የሠራዊት ግንባታ ይቀጥላል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ፣ ተመራቂ መኮንኖቹ ከነባሮቹ ጋር በመቀናጀት ኃላፊነታቸውንና ተልእኳቸውን እንዲወጡ አስገንዝበዋል።

ተመራቂዎቹ እንደእሳት ተፈትነው የወጡ፣ በሽምቅ ውጊያ የበቁ፣ ውትድርናን ያጣጣሙና የሀገርና የሕዝብን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ በላቀ አፈጻጸም የተመረጡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

መኮንኖቹ ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆኑ እና ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት እና ከብሔር ውግንና የጸዱ መሆናቸው የተረጋገጠ እንደሆነም አመልክተዋል።

የማህበራዊ ሳይንስ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ እና ወታደራዊ ጥበብ እና እውቀት ያላቸው መሆኑ የተመሰከረላቸው እንደሆኑ ጠቁመዋል።

ተመራቂዎቹ ጥብቅ ሥነ ምግባርን የተላበሱ መሆናቸውን የጠቆሙት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ለአመራርነት የበቁ፣ አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ብቃት ያዳበሩ ናቸውም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የልማት እና የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ላይ እንደምትገኝ በመጠቆም፣ አሁን ከተደረሰው በላይ ለመጎናጸፍ ተመራቂዎቹ የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አሳስበዋል።

እየተመዘገበ ያለውን ልማት ለማደናቀፍ የውስጥ ጸረ ሰላም እና ጽንፈኛ ኃይሎች ውጭ ካሉ የኢትዮጵያን ሰላም መስፈንና ልማትን ከማይሹ ኃይሎች ጋር በማበር የሚንቀሳቀሱ መኖራቸውን ገልጸዋል። እነዚህ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡም አሳስበዋል።

ተመራቂ መኮንኖቹ የእነዚህን ጸረ ሰላም እና ጽንፈኛ ኃይሎችን እንቅስቃሴ በመመከት የሀገርን ሰላም ደህንነት ማስጠበቅ እና ጥቅም ማሳካት እንደሚገባም ተናግረዋል።

በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችም በተቀነባበረ መልኩ የሚደረግ የሥነ ልቦና ጦርነትን ጭምር በመመከት የኢትዮጵያ የከፍታ ጉዞ እንዲሳካ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል።

ተመራቂዎቹ የቀሰሙትን ወታደራዊ ሙያ ከነባር ሠራዊት ተሞክሮ ጋር በመደመር በፈተና ውስጥ ፈጥኖ በመወሰንና ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል ብቃት ማዳበር እንደሚኖርባቸው አመልክተዋል።

ተመራቂ መኮንኖቹ በበኩላቸው፤ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማስጠበቅ እንደሚሰሩ፣ የሚሰጣቸውን ሀገራዊ እና ወታደራዊ ተልእኮ ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን በተወካያቸው በኩል ባስተላለፉት መልእክት ተናግረዋል።

የተመራቂ መኮንኖች ተወካይ ምክትል መቶ አለቃ በላቸው ካሳሁን መመረቃቸው እድልም ድልም መሆኑን ተናግረዋል።

ንጹህ የሀገር ፍቅር ስሜት በመላበስ እልህ አስጨራሽ የሆነውን ስልጠና መወጣት መቻላቸውን አመልክተው፤በስልጠናው ወታደራዊ እና ሥነ ልቦና ብቃት መላበስ እንደቻሉም ነው የገለጹት።

በሀገራችን ክብር የማንደራደር መሆናችንን ከአባቶቻችን ተምረናል ያሉት ምክትል መቶ አለቃ በላቸው፤ሰላም ለማሳጣት፣ ልማትን ለማደናቀፍ የሚጥሩ የጽንፈኞችን ቅዥት ለማምከን ቁርጠኞች ነን ብለዋል። የሚሰጣቸውን ሀገራዊና ወታደራዊ ተልእኮ ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

# ትኩረት የሚሻው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚዳርግ መሆኑን አንስተው፤ ከዛ ይልቅ በሥነምግባር ጉድለት ሳቢያ ሊከሰትባቸው የሚችለውን ጉዳቶች በተረጋጋ ሁኔታ ማስረዳትና ወደ ትክክለኛው መስመር መምራት እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ተማሪዎችን በእውቀትና በሥነ ምግባር ለማነጽና ብቁ ዜጋ ለመፍጠር ወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎች ተቀናጅተው መሥራት እንዳለባቸው ይጠቅሳሉ፡፡

ለልጆቹ የሚያስብ ወላጅ ከሌለ ለራሱ የሚያስብ ወጣት መፍጠር አዳጋች እንደሚሆን የሚናገሩት ደግሞ የሥነልቦና ባለሙያና የህይወት ክህሎት አሰልጣኝ የሆኑት ወይዘሪት ፍረወይኒ ረታ ናቸው፡፡ እንደሳቸው አባባል፤ ቤተሰብ ወይም አሳዳጊ የኑሮ ሁኔታ፤ የልጆች በአስተዳደግ ወቅት ፍቅር ማጣት፣ የአትችሉምና የበታችነት ስሜት ልጆች ላይ መፍጠር በአጠቃላይ ከቤተሰብ ጋር በላላ ግንኙነት ያደጉና የኖሩ ተማሪዎች በአብዛኛው ወደ አልተገባ መንገድ እንዲገቡ የሚገፉ ምክንያቶች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

ተማሪዎች በሌሎች ዘንድ እውቅና ለማግኘትና በሚሰማቸው የበታችነት ስሜት በጎ ወዳልሆነ ተግባር ለመሰማራት እና የአቻ ግፊት ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ይጠቅሳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች በመጠጥ ፣ በጫት እንዲሁም በሌሎች ሱስ አምጪ ተግባራት ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል፡፡

በትምህርት ሰአታት ትክክል ባልሆነ መንገድ ከትምህርት ቅጥር ግቢ በመውጣት ቁማር ቤት የሚሄዱት በአብዛኛው የቤተሰብ ፍቅር እጦት ያለባቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በአሉታዊ የአስተዳደግ ዘይቤ ምክንያት ከባህልና ሥርዓት ባፈነገጠ መልኩ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ላልተገባ ነገር ሲያውሉ የሚስተዋል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ የቁጣና በዱላ የእርምት እርምጃዎች ተማሪዎችን ለእልህና ለበቀል ብሎም ሌላ ሰው ላይ ጫና ለማድረስ ከመሞከር ባለፈ መፍትሄ እንደማይሆን አንስተው፤ተማሪዎች ያልተገባ ባህሪ ቢያሳዩ እንኳን በምክርና በንግግር መፍታት ይገባል ነው ያሉት፡፡

በትምህርት ሰአት ከትምህርት ገበታው ውጪ የሆነ ተማሪ ሲያገኝ ለመገሰጽ መምህር ወይም ወላጅ መሆን አይጠይቅም ያሉት ወይዘሪት ፍረወይኒ፤ ሁሉም በኃላፊነት ለምን ብሎ ከመጠየቅ ጀምሮ ስርአት እንዲይዙ መምከር አለበት ባይ ናቸው፡፡

የሥነልቦና እና የማህበራዊ ጉዳዮች ባለሙያ የሆኑት አቶ ዳዊት ላቀው በበኩላቸው፤ ለተማሪዎች የሥነምግባር ችግር መንስኤ በዋነኝነት የወላጆች አስተዳደግ መንገድ ነው ይላሉ፡፡

አንዳንድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ባልተገባ ቦታና ጊዜ ለተለያዩ ሱሶች ተጋልጠው ይታያሉ፡፡ ለዚህም በእድሜ ከሚከሰት ባህሪ በተጨማሪ የወላጅ አስተዳደግ፣ የአቻ ግፊት፣ በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሱስ ማዘውተሪያዎች መብዛት እና የትምህርት ቤት አስተዳደር ማነስ እንደምክንያት የሚጠቀስ መሆኑንም ያነሳሉ፡፡

አቶ ዳዊት እንደሚናገሩትም፤ ከወላጆቻቸው የሚሰጣቸው አላስፈላጊ ገንዘቦች ወደ ሱስ የሚ ያስገባቸው ሲሆን፤ ለሱሳቸው የሚሆን ገንዘብ የሌላቸው ደግሞ በስርቆት ላይ ይሰማራሉ፡፡

ይህን የልጆች ያልተገባ ባህሪ ደግሞ የመግራት የወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ኃላፊነት ነው፡፡ከቤት ውስጥ ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ያላቸውን እንቅስቃሴ መከታተልና የባህሪ ለውጥ ሲያስተውሉ "ሳይቃጠል በቅጠል" እንዲሉ ተከታትሎ በአጭሩ በመልካም ስብእና ማነጽ ይገባል፡፡ በተለይ ወላጆች በጣም ጥብቅ እና ልቅ ባልሆነ አስተዳደግ በሥነምግባር በትምህርታቸው ልጆቻቸውን የበቁ ማድረግ አለባቸው ነው ያሉት፡፡

የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች በመልካም ሥነምግባር ታንጸው ማደግ ለአንድ ሀገር ብቁ ሀገር ተረካቢ ትውልድን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ በመልካም ሥነምግባር የታነጹ ወጣቶችን ለማፍራትም ሁሉም ድርሻ ያለው ቢሆንም ቤተሰብ፣ትምህርት ተቋማት፣መገናኛ ብዙሀን እና የሃይማኖት ተቋማት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# "አህጉራዊ ነፃ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተናግረዋል።

አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን አፍሪካውያንን በአንድ ጠንካራ የገበያ ሥርዓት ማስተሳሰር ተገቢ ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ታዬ፤ ነጻ የንግድ ቀጣናው አፍሪካውያንን በማስተሳሰር ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ ያግዛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ አዲስ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ለውጭ ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ ፈጥራለች፤ የአፍሪካ የንግድ ቀጣናም እንዲተገበር ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸው፤ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና በአህጉሩ ውስጥ የንግድ ትስስርን በማፋጠን የኢኮኖሚ ትብብር እንዲመጣ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ነጻ የንግድ ቀጣናው ከምንም በላይ አፍሪካ በዓለም መድረክ ተሰሚነቷ ከፍ እንዲል ያስችላል። እንዲሁም በአፍሪካ ሀገራት መካከል የሚኖረው የንግድ ትስስር እንዲጠናከር፣ የጾታ እኩልነትን ለማምጣት፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ድህነት ለመቀነስ አይነተኛ መሳሪያ ነው። የነፃ የንግድ ቀጣና በሙሉ ሲተገበር ሀገራቱን በማቀራረብ ትልቅ አቅም ይኖረዋል።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ዋና ጸሐፊ ዋምኬሌ ሜኔን በበኩላቸው፤ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ትግበራ በጥሩ ሂደት ላይ ነው። ትግበራውን በብሄራዊ ደረጃ በማፋጠን ጥራት ያለው ምርትን በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፤ የአፍሪካን ገበያ ወደ አንድ ለማምጣትም ይረዳል ብለዋል።

ነጻ የንግድ ቀጣናው ሙሉ በሙሉ ወደ ትግበራ እንዲገባ የሁሉም ሀገራት ጥረት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፤ ነጻ የንግድ ቀጣናውን ለመተግበር በሚደረገው ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያ በጥሩ ሂደት ላይ እንደምትገኝም ገልጸዋል።

እንደ ዋና ጸሐፊው ገለጻ፤ ወጥነት ያለው የገበያ ሥርዓት በመፍጠር የበለጸገች አፍሪካን እውን ማድረግ አስፈላጊ ነው። የግሉን ዘርፍ ተዋንያን በማሳተፍና የዲጅታል ንግድን ማቀላጠፍ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። የአፍሪካን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል በአፍሪካውያን መካከል ያለውን ንግድ በእጥፍ ወይም ከዚያም በላይ ማሳደግ ተገቢ ነው።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና የአገልግሎትና የእቃዎችን አንድ የጋራ ገበያ ለመፍጠር ከፍተኛ እድል ያመጣል። በአባል ሀገራት መካከል ንግድን በማሳለጥ ትስስርና በጋራ እንዲያድጉ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ በሚደረጉ ትብብሮች፣ ድህነት ቅነሳ፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ በኢንዱስትሪያላይዜሽንና የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ከአባል ሀገራት ጋር በጋራ በመቆም የበኩሏን ሚና ትወጣለች ብለዋል። ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማሻሻያው ነጻ የአፍሪካ የንግድ ቀጣናውን ለማሳለጥ ይረዳል ነው ያሉት።

# የሕይወት ገጽታ

# የሀገር ባለውለታው አትሌት ፀጋዬ ሳኒ

**ዓመለወርቅ ከበደ**

አትሌት ፀጋዬ ሳኒ፤ ለውትድርና የወጡት የሀገርን ጥሪ ተቀብለው የጥቂት ወራት ትዳራቸውን ጥለው ነበር። በቆይታቸውም ሀገር የጠላት ኃይልን ለማባረር ባደረገችው ጥረት ላይ የራሳቸውን ዐሻራ አሳርፈዋል። በትግል ወቅትም ከመረብ፤ በቦምብ ፍንጣሪ ተመትተው እስከ መቁሰል የደረሰ አደጋ አጋጥሟቸዋል።

በውትድርና ለሀገር መስዋዕትነት ከመክፈል ባለፈ፤ በአትሌቲክስ በተለያዩ የአፍሪካ እና የዓለም መድረኮች በመወዳደር የኢትዮጵያ ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አድርገዋል። ሁለት ጊዜ የደረሰባቸው አደጋ ከእሩጫ ውድድር አላስቆማቸውም። በዛሬ ገጻችን በውትድርና በአትሌቲክስ ያሳለፉትን የሕይወት ውጣ ውረድ እና ያስመዘገቡትን ድል በተመለከተ አቅርበንላችኋል።

አትሌት ፀጋዬ ትውልድና እድገታቸው አርሲ ክፍለ ሀገር ጭላሎ አውራጃ ኮፈሌ ወረዳ ሽሬ አራጌሴ ቀበሌ ነው። ከአንድ ገበሬ ቤተሰብ በ1948 ዓ.ም ቢወለዱም፤ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ተምረዋል። ቀጥለው ወደ መደበኛ ትምህርት የገቡ ሲሆን፤ በወቅቱ በአካባቢው ትምህርት የሚሰጠው እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ ስለነበር ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ ያለውን የትምህርት ደረጃ አክስታቸው ጋር አርሲ ሄደው እስከ ዘጠነኛ ክፍል ተምረዋል።

አትሌት ፀጋዬ እንደገለፁት፤ በ1968 ዓ.ም የደርግን መንግሥት በመቃወም በተካሔደ አድማ ትምህርት ቤቶች ተዘጉ። በወቅቱ ተማሪው፣ ወጣቱ ይገደል ስለነበር፤ የእርሳቸውም አብሮ አደግ ጓደኛቸው ተገደለባቸው። በዚህ ምክንያት ይበልጥ የተቃውሞው ተሳታፊ ሆኑ። ነገር ግን አባታቸው «አልፈልግም ልጄን ይገድሉብኛል» ብለው አትሌት ፀጋዬን ወደ ቤት ወሰዷቸው።

እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በወቅቱ የነበሩ ጓደኞቻቸው ጭምር ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲገቡ ተደረገ። ገጠር ከተመለሱ በኋላ ለጥቂት ጊዜያት አባታቸውን በእርሻ ሥራ እያገዙ ቆይተው፤ የንግድ ሥራ መሥራት ጀመሩ። በወቅቱ የመሬት ባለእርስት የነበሩ ሰዎች የጦር መሣሪያ ስለነበራቸው ትጥቅ እንዲፈቱ ይደረግ ነበር። ስለዚህ ባለርስቶችን ሁሉንም ሰብስበው እስር ቤት ወሰዷቸው። እርሳቸውም ከተማ ቆይተው ሲመለሱ ኢሕአፓ ናቸው፤ ትምህርት ቤት እረብሸው መጥተዋል ተብለው ታሰሩ።

"አንድ ሳምንት ከታሰርኩ በኋላ፤ አባቴ በዛም በዚህም ብሎ አስፈታኝ። የዛኔ እህቴ ልታገባ ነበር። የእርሷ ሠርግ ካበቃ በኋላ እኔንም ማግባት አለብህ አሉኝ። ትዳር አልይዝም ወደ ትምህርት ቤት እመለሳለሁ ብላቸውም፤ የምትመለሰው ለመሞት ነው? አትመለስም የምታገባትን ሴት ምረጥ አሉኝ። ከእኛ ቤት ከፍ ብሎ የአንድ ባለእርስት ልጅ ነበረች፤ እሷን መረጥኩ፤ ሽማግሌ ተላከና ተጋባን።" በማለት ይገልጻሉ።


ከሚስታቸው ጋር የቆዩት ለስድስት ወራት እድሜ ብቻ ነበር። በ1969 ዓ.ም ሶማሊያ ኢትዮጵያን በመውረሯ በኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም በሚዲያ ጥሪ ተደረገ። እርሳቸውም ጥሪውን ተከትለው ዘመቻውን ተቀላቀሉ"።

ስለተመዘገብክ ትዘምታለህ አሉኝ፤ እምቢ ብዬ ብቀር ሌላ ችግር ነው። በዛ ላይ ደግሞ የሀገር ጉዳይ ነው። አባቴም አርበኛ ስለነበር ዝመት ልጄ አለኝ። አባቴ ቀድሞ በጦር ሜዳ ያለውን ነገር ስለሚያውቅ፤ ልጄ በጦር ሜዳ ላይ የሚያጋጥመው ብዙ ነገር ነው ። ስለዚህ መሣሪያ ይዤያለሁ ብለህ ንጹሓንን እንዳትገድል፣ የሰው ንብረት እንዳትነካ፣ ሴት ልጅ እንዳትደፍር ብሎ መከረኝ። "ይላሉ።

ዘመቻውን ከተቀላቀሉ በኋላ የሥልጠና ጊዜያቸውን አጠናቀው፤ ወደ ግንባር ለመሄድ እየተዘጋጁ እያለ የደርግ አባል የሆኑ አንድ ባለሥልጣን ሰልፉን ሲጎበኙ እርሳቸውን ተመለከቱና፣ "አንተ ገበሬ ነህ እንዴ?" ብለው ጠየቋቸው። እርሳቸውም መልሰው ገበሬ እንደሆኑ ገለጹላቸው።

ቀልጣፋነታቸውን ስለተመለከቱ ገበሬ ነኝ በሚለው ምላሽ ውስጣቸው አላመነም ነበር። በኋላም ወደ አንድ ሻለቃ አምጥተው ድጋሚ ሲጠይቋቸው መልሳቸው ተመሳሳይ ሆነ፤ እስከ ስንተኛ ክፍል እንደተማሩ ሲጠይቋቸው እስከ ሦስተኛ ክፍል ብለው መለሱላቸው።

ምክንያቱም ይላሉ አትሌት ፀጋዬ፤" ተማሪ ሆነው፤ ኢሕአፓ ሆነው ሠራዊት ውስጥ ተቀላቅለው ሠራዊቱን ሊቀሰቅሱ ይችላሉ የሚል ፍራቻ ነበራቸው። አንድ ከኔጌሌ ቦረና የመጣ ጓደኛ ነበረኝ፤ እርሱም ትምህርቱን ያቋረጠው ከ10ኛ ክፍል ነው ። ኬኒያ አካባቢ ስለነበር እንግሊዘኛ ቋንቋ አቀላጥፎ ይናገራል። እሱም እኔም ያቋረጥነው ከሦስተኛ ክፍል ነው ብለን ተናገርን።" ይላሉ።




እርሳቸው እና ጓደኛቸው የሬዲዮ ኦፕሬተር እንዲሆኑ ሥልጠና ተሰጣቸው። ሰኔ 18 ቀን 1969 አዲስ አበባ ከተማ ሰልፍ ካሳዩ በኋላ፤ በማግስቱ በአውሮፕላን ተጭነው ድሬዳዋ ከተማ ሄዱ። ወደ ከተማው ሲደርሱ፤ በከተማው ዙሪያ የተኩስ ድምፅ ስለተሰማ ወደ ሐረር ሄዱ። ከሐረር በመኪና ወደ ጂግጂጋ ገብተው ዙሪያ ጥበቃ አደረጉ።

እነርሱ ሐምሌ ወር ገብተው፤ ነሐሴ 26 ሶማሊያ ጅግጅጋን ለመያዝ ከባድ ውጊያ እንደከፈተች የሚናገሩት አትሌት ፀጋዬ፤ ወቅቱ የነበረውን አሰቃቂ ሁኔታ በአዕምሯቸው ወደ ኋላ ሄደው ሲያስታውሱ፤" ከተማ ወስጥ የነበሩ ነዋሪዎች ከከተማው ሲያፈገፍጉ አንድ ሴት አንድ ልጅ በእጇ ይዛለች፤ አንዱን በጀርባዋ አንዱንም ለመሸከም ትሞክራለች፤ አሮጊቶችም ይሮጣሉ። በዛ መሐል ከባድ መሣሪያ እንደጉድ ይወርዳል።» በማለት ይገልጻሉ።

"እኛ ውስን እግረኛ ጦር ነበረን፤ በብዛት የነበረን አየር ኃይሉ ስለሆነ፤ ሽፋን የሚያደርግልን እነሱ ናቸው። በጦርነቱ ሬዲዮ ይዤ መልዕክት እየተቀበልኩ ለሠራዊቱ እያስተላለፍኩ ሠራዊቱ ጥሎኝ አፈገፈገ። ከዛን ብቻዬን ተቆርጬ ቀረሁ። ወደ ካራማራ አፈገፈግን፤ መልሶ ማቋቋም ከተደረገ በኋላ አንድ የደርግ ባለሥልጣን መጥተው አበረታቱን። አጋዥ ኃይል ደረሰልን ከሰዓት በኋላ መልሶ ማጥቃት ጀምረን ጅግጅጋን አስለቅቀን ወደ ነበሩበት መለስናቸው።" ይላሉ

ባስለቀቁበት ቦታ ለአንድ ሳምንት በመከላከል ቆዩ። ነገር ግን ከባድ መሣሪያ ስለጠነከረባቸው በመንግሥት ትዕዛዝ ቦታውን ለቀው እንዲወጡ ተደረገ። በሚወጡበት ወቅት መንገድ ላይ ጥይት ጭኖ የሚጓዝ ሦስት የጠላት መኪና አግኝተው በውስጡ ያሉ ወታደሮችን ገድለው መኪናዎቹ ማቃጠላቸውን እንደገጠመኝ ያነሳሉ።

በእዛው መንገድ ላይ እያሉ ሌላ ክስተት እንዳጋጠማቸው የሚያነሱት፤ "ከተማውን በጀርባችን ጥለን ወደ ካራማራ ጥግ ስንሄድ ሁለት የጠላት ታንክ ቀድሞን ነበር። ከዛን ሰማያዊ ባንዲራ አወጣ። ሰማያዊ ባንዲራ ማውጣት እጅ ስጡ ማለት ነው። ቀድመን አንዱን ታንክ ስንመታ፤ ለካስ ከፊት ለፊታችን እግረኛ ጦር ነበር። እነሱን ስንሸሽ ደግሞ ከፊት ለፊታችን ስድስት የጠላት ታንክ እየመጣ ነው። እንደ ዕድል አየር ኃይል መጣልን፤ ሁለቱ ታንኮች ሲቃጠሉ ሌሎች ጥለው ሸሹ። በዚህ ሁኔታ ጠላትን አስለቅቀን ካራማራን በጥሰን ወጣን።" ሲሉ ይናገራሉ።

አትሌት ፀጋዬ እንደሚናገሩት፤ ቆሬ ግንባር ላይ መሽገው በነበረበት ወቅት በቀለብ እጦት ብዙ ተቸግረዋል። በወቅቱ በወንዝ ዙሪያ ስለነበሩ፤ የውሃ ችግር ባያጋጥማቸውም፤ የሐረር ዙሪያ ተከቦ ስለነበር ቀለብ በአውሮፕላን እየመጣላቸው በፓራሹት ይወርድላቸው ነበር። በዚህ ሁኔታ ደግሞ ሁሉንም ሠራዊት በበቂ ሁኔታ ማድረስ አስቸጋሪ ነበር። አውሮፕላኑ ሲወረውር ነፋስ ወስዶ ለጠላት ሰጥቶባቸውም ያውቃል።

እዛው ቆሬ ግንባር እየተዋጉ አለቃቸው በማስተባበር ላይ ሳሉ ደረታቸው ላይ ተመትተው ወደቁ። አትሌት ፀጋዬ ሕይወታቸውን ለማዳን በአዕምሯቸው የመጣላቸውን አማራጭ ተጠቅመው፤ ቀና አደረጓቸውና የተመቱበትን ቦታ በጨርቅ ቢያስሩላቸውም፤ ነፍሳቸውን ማዳን አልተቻለም።

ሬዲዮኑን አንስተው ለአዛዦቻቸው በምስጢራዊ ቃል የአስተባባሪው ሕይወት ማለፉን ገልጸው፤ እርሳቸው ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ እና እንዲያስተባብሩ ተደረገ። መልሶ ማጥቃት ተጀምሮ የሱማሊያን ጦር እንዲያፈገፍግ ካደረጉ በኋላ፤ ግንባር ላይ ባሳዩት ቁርጠኝነት በጦሩ ውስጥ ተወዳጅነትን ማትረፍ ቻሉ።

ድል አድርገው ኦጋዴንን ካስለቀቁ በኋላ አትሌት ፀጋዬ የነበሩበት ሦስተኛ ክፍለ ጦር የቀድሞ መሪ የመንግሥቱ ኃይለማሪያም ክፍል ሆነ። የጦር ሜዳ ታሪካቸው በምሥራቅ ብቻ አላበቃም። ከምሥራቅ ግንባር ከተመለሱ በኋላ በሰሜን ግንባር ተሰልፈው ዘምተዋል።

"የዛኔ 95 በመቶ የሚሆነው የኤርትራ ክፍል በሻቢያ ቁጥጥር ስር ነበር። በሰሜኑ ጦርነት የዘመትኩት በአዲግራት በኩል ሲሆን፤ እኛ በአዲግራት በኩል እያጠቃን እያስለቀቅን አሥመራ ገባን። በምፅዋ በኩል ያለው ጦርም እያጠቃ ወደ አሥመራ ከአሥመራ ወደ ከረን መጣ። ከአምስት ወር ቆይታ በኋላ ናቅፋ ገባን። ከዛ በኋላ አልጌና በሚባልበት አካባቢ ለሰባት ዓመት ኖሬያለሁ።" ይላሉ።

ልጅ እያሉ በትምህርት ቤቶች የእሩጫ ውድድር ላይ ይሳተፉ እንደነበር በመጥቀስ ወደ አትሌቲክሱ እንዴት ሊቀላቀሉ እንደቻሉ ያነሳሉ። አልጌና በነበሩበት ወቅት ቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆነው የስፖርት ወሬዎችን ያዳምጣሉ። እነ ምሩፅ ይፍጠር ተወዳድረው ያሸነፉበትን ዜና ሲሰሙ እንደልጅነታቸው በስፖርት ሊቀጥሉ ባለመቻላቸው ውስጣቸው በቁጭት ይንገበገባል።

በ1973 ዓ.ም የጦር ኃይሎች ውድድር ይካሄዳል ተብሎ የተለያዩ የስፖርት ሜዳዎች ተዘጋጁና ሩጫ የሚችል በሩጫ፣ እግር ኳስ የሚችል በእግር ኳስ፣ ሌሎች የስፖርት አይነቶችን የሚችሉም እንደዛው ልምምድ እንዲያደርግ ተደረገ። እርሳቸውም በሩጫ ለመሳተፍ ሲጠይቁ መቶ መሪ በመሆናቸው የሳቸውን ኃላፊነት የሚወስድ ስለሌለ አይቻልም ተብለው ነበር።

ነገር ግን ሻምበል ድጋፌ የሚባሉ አዛዣቸው በቀለም ትምህርታቸውም ዩኒቨርስቲ ቀመስም ስለነበሩ ተስፋ እንዳይቆርጡ ያበረቷቷቸው ነበር። አትሌት ፀጋዬ የነበሩበት አካባቢ በጣም ሞቃት ስለነበር ልምምድ ሲያደርጉ የሚመለከቷቸው ሰዎች "በዚህ ሙቀት ስትሮጥ ቀልጠህ እንዳትቀር" የሚሏቸው ቢሆንም፤ ወደፊት መሮጥን ብቸኛ አማራጫቸው አድርገው ወሰዱ።

እዛው ጦር ውስጥ በሻለቃ ደረጃ ውድድር ሲደረግ በ5000 እና 10 ሺህ ሜትር አንደኛ ወጥተው አሸነፉ። ቀጥሎም በብርጌድ ደረጃ በተደረገ የሩጫ ውድድር በተመሳሳይ ደረጃ አሸነፉ። በ1974 ዓ.ም በ10ሺህ እና ግማሽ ማራቶን ተወዳድረው በአንደኝነት አጠናቀቁ።

"ከዛ በኋላ አሥመራ ከተማ ለውድድር ለመሄድ እየተዘጋጀን እያለ ቀይ ኮከብ ዘመቻ የሚባል ሲመጣ ወደ ውጊያ ገባሁ። በጦርነቱ በቦንብ ፍንጣሪ እግሬን ተመትቼ ስለቆሰልኩ ሆስፒታል ተኛሁ። ስድስት ወር ታክሜ ድኜ ወጣሁ። ከዛ በፊትም አሥመራ ዙሪያ ተመትቼ የወጣሁት ለአራት ወር ሆስፒታል ተኝቼ ነው።" ሲሉ ይናገራሉ።

የደረሰባቸው አደጋ ከአትሌቲክስ መንደር ሊያጠፋቸው አቅም ያገኘ አይመስልም። ከደረሰባቸው አደጋ ለስድስት ወራት ከልምምድም ሆነ ከውድድር ቢገለሉም፤ መልሰው የስፖርትን በር ከማንኳኳት አልተገደቡም። ከዳኑ በኋላ ተመልሰው ልምምድ ማድረግ ጀመሩ።

በ1976 ዓ.ም በአሥመራ ከተማ የተለያዩ ውድድሮች ሲደረጉ ያሉበትን ዕዝ ወክለው ለመወዳደር ዕድሉን አገኙ። ነገር ያየር ሁኔታው እርሳቸው ከለመዱት ሞቃት አየር ተቃራኒ ስለነበር ድል ሳይቀናቸው ተመለሱ።

"በ1977 ዓ.ም እኔ እና አንድ ልጅ አሥመራ ተጠርተን መጣን። የጠሩን ጄኔራል ‹ጎበዞች እንደሆናችሁ አይቻለሁ እና አሁን የምታደርጉት ውድድር ሦስት ኪሎ ሜትር ትጥቅ ይዞ መሮጥ፣ ስድስት ሜትር መሰናክል መዝለል ነው።› ተባልን። መሰናክሉን ስንዘል ሦስት ሜትር ጉድጓድ አለ፤ ካመለጥን እዛ ጉድጓድ ውስጥ ነው የምንገባው። ይህን ውድድር በጥሩ ሁኔታ ተለማመድኩና አንደኛ ወጣሁ።" ሲሉ ይናገራሉ።

በእዛ ዓመት አዲስ አበባ ላይ ይደረጋል የተባለው ውድድር ለቀጣይ ዓመት ተዛወረ። እርሳቸውም ከነበሩበት የአልጌና ክፍለ ጦር ወደ ምፅዋ ተዘዋወሩ። ወደ ምፅዋ ከተዘዋወሩ በኋላ ወደ ግንባር እንዳይሄዱ ተደረገና ሚሊተሪ ፖሊስ አዛዥ ሆነው መሥራት ጀመሩ። በዚህም የነበራቸው ኃላፊነት ምፅዋ ወደብ አካባቢ ሰርጎ ገብ ጀልባዎችን በመቆጣጠር እና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# የሀገር ባለውለታው...

ከገጽ 6 የዞረ

በተሠራችው ነጯ ቤተመንግሥት ጠዋት ጠዋት በክቡር ዘበኛ ታጅበው ባንዲራ ማሰቀል ነው።

ምፅዋ ላይ እንደዚህ እየሠሩ እያለ በ1978 ዓ.ም ባሬንቱን ጠላት አጠቃ። ተዋግተው ካስለቀቁ በኋላ ተመልሰው ወደ ነበሩበት አልጌና ገቡ። በዛው ዓመት ጥር ላይ በአስቸኳይ ወደ አሥመራ እንዲላኩ ቴሌግራም ተላከ። ሲመጡ በደንብ ተለማመድ ጦር ኃይሎች አዲስ አበባ ውድድር ይካሄዳል ተባሉና ልምምድ ጀመሩ።

ውድድሩን ለመሳተፍ ሚያዚያ ወር ላይ ወደ አዲስ አበባ መጥተው፤ በውድድር ውጤታማ ስለሆኑ አዲስ አበባ ቀርተው ለአንድ ዓመት ልምምድ ካደረጉ በኋላ በኢትዮጵያ አትሌትክስ ፌዴሬሽን ለብሔራዊ ቡድን ተመረጡ።

አትሌቱ በማራቶን መወዳደር ጀምረው ስለነበር የመላው አፍሪካ ጨዋታ በኬኒያ ስለሚደረግ፣ በዛ ለመወዳደር የሰዓት ሙከራ ውድድር ማድረግ እንደሚፈልጉ ለአሠልጣኛቸው ተናግረው ተፈቀደላቸው። በውድድሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተወዳደሩ አትሌቶች ከነመሐመድ ከድርና ሌሎች አትሌቶች ጋር ተወዳድረው በአንደኛነት አጠናቀቁ።

በውድድሩ ባልተጠበቀ ሁኔታ በማሸነፋቸው በጣም ተወራላቸው። የታቀደው የኬኒያው ውድድር ቀረና የአበበ ቢቂላ ወድድር በወቅቱ ዓለም አቀፍ ስለነበር በዛ ውድድር ተሳትፈው በሦስተኛነት አሸነፉ።

በውድድሩ አሸናፊ መሆናቸውን ተከትሎ ከብሔራዊ ቡድን ደመወዝ ተቆራጭ እየተደረገላቸው መሮጥ ጀመሩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ሄደው የመወዳደር ዕድል አገኙ። በማራቶን ውድድር አልጀርስ ከተማ ላይ ተሳትፈው አራተኛ ሆነው አጠናቀቁ።

በወቅቱ በአልጀርስ ከተማ የነበረው ሙቀት ከፍተኛ እንደነበር የሚያስታውሱት አትሌቱ፤ ሙቀቱ በጣም ከፍተኛ ስለነበር የሮጡት አመሻሽ ላይ ነበር። ውድድሩ አመሻሽ ላይ ቢደረግም ሁሉም አትሌት በሚባል ደረጃ ሙቀቱን ስላልቻሉ ከእርሳቸው ጋር አራት አትሌቶች ብቻ ውድድሩን አጠናቀቁ። ወድድሩን ሲመሩ ቆይተው በመጨረሻው ደቂቃ በመዘናጋታቸው ከኋላቸው መጥተው ሦስቱም ቀድመዋቸው ገቡ።

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1989 በጃፓን ቶኪዮ ከተማ በተደረገ የማራቶን ውድድር ተሳትፈው የዲፕሎማ ደረጃ ይዘው አጠናቀዋል። ከዛ ከተመለሱ በኋላ በአበበ ቢቂላ ውድድር ተሳትፈው ሦስተኛ ደረጃ ይዘው አጠናቀቁ። ወደ ናይጄሪያ ሄደው በማራቶን እየተወዳደሩ አንድ ክስተት እንደገጠማቸውም አጫወቱን።

"አንድ የናይጄሪያ አትሌት በጣም እየተፎካከረ ስለነበር እርሱን ለማዳከም ወጣ አልኩኝ። በዛ መሐል በሞተር ሳይክል የሚመራን የተሳሳተ አቅጣጫ አሳይቶኝ በተሳሳተው መንገድ እሩጫዬን ተያያዝኩት። እኛን የሚከታተሉ እዛ የሚኖሩ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ስለነበሩ እነሱ መኪና ይዘው ይከታተሉናል ነበርና "ፀጋዬ፣ ፀጋዬ!" ብለው ሲጠሩኝ፤ ዞር ብዬ ስመለከታቸው መንገዱ በዛ እንዳልሆነና ወደ ግራ እንድዞር ነገሩኝ።" በማለት ይናገራሉ።

ወደ ግራ ሲመለሱ አትሌቶቹ እየሮጡ ተመለከቱ፤ ያላቸውን ኃይል አሟጠው በመሮጥ እየመራ ወዳለው አትሌት ደረሱ። እርሳቸውን ተከትለው ሌሎች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ደረሱ። እርሳቸው አንደኛ ሲወጡ ሁለቱ የኢትዮጵያ አትሌቶች፤ አትሌት ከበደ ባልቻ እና የኃይሌ ገብረሥላሴ ወንድም ተኬ ገብረሥላሴ ሁለተኛና ሦስተኛ ወጥተው ኢትዮጵያ ከአንድ እስከ ሦስት ያለውን ደረጃ ይዛ አሸነፈች።

አትሌቱ መንገድ ስተው ከሄዱ በኋላ ተመልሰው በማሸነፋቸው፤ አበረታች መድኃኒት ወስደዋል በሚል ጥርጣሬ ውድድሩን እንዳሸነፉ፤ ምርመራ ተደርጎላቸው አለመውሰዳቸው ተረጋግጦ ሽልማታቸውን ለመውሰድ ችለዋል። በአጠቃላይ በውድድሩ ኢትዮጵያ ሁለት ወርቅ ስታገኝ አንዱን ያስገኙት እሳቸው ናቸው።

አትሌቱ ኢትዮጵያ ከመወከል አልፈው አፍሪካን ወክለው በአውሮፓ በሚደረግ ውድድር ለመሳተፍ ታጭተው ነበር። ለዛም ውድድር ልምምድ እያደረጉ እያለ፤ ኢትዮጵያ ከእሥራኤል ጋር ዲፕሎማሲያው ግንኙነት በምትመሠርትበት ቀን ኢትዮጵያን ወክለው እንዲሮጡ ከወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጥቆማ ተጠሩ።

አፍሪካን ወክሎ መሮጡ ትልቅ ዝና ያለው ቢሆንም፣ ሀገራቸውን ለማስቀደም በማሰብ በእሥራኤሉ ውድድር ለመሳተፍ ወሰኑ። ወድድሩ በተመሳሳይ ወቅት ስለነበር አፍሪካን ወክሎ መሮጡ ቀርቶ፣ ወደ እሥራኤል አቀኑ። በዛም ወድድር ድል ቀንቷቸው ሦስተኛ ወጥተው አሸነፉ።

የኢጣሊያ መንግሥት አበበ ቢቂላ ያሸነፈበትን ቀን በየዓመቱ በሩጫ ያከበር ስለነበር፤ በሮም አበበ ቢቂላ ያሸነፈበት 30ኛ ዓመት ሲከበር እርሳቸውም በሩጫ ውድድሩ ለመሳተፍ ከሌሎች አትሌቶች እና የክብር እንግዶች ጋር ወደ ሮም አቀኑ። በውድድሩ እርሳቸው ስድስተኛ ቢወጡም፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከአንድ እስከ ስድስት ያለውን ደረጃ ይዘው አሸነፉ።

ከአንድ ዓመት በኋላ እሥራኤል ሀገር ለውድድር ተጠርተው በመሄድ በአንደኛነት አሸነፉ። ከውድድሩ ሲመለሱ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ተደረገ። የሚደረግላቸው የደመወዝ ድጎማም ተቋረጠ፤ ይህን ተከትሎ አጠቃላይ የነበረው የአትሌቲክስ ስሜታቸው ተቀዛቀዘ።

የደመወዝ ተቆራጩ ቢቋረጥም አትሌቱ ያለውን ነገር አቻችለው ልምምዳቸውን ቀጥለው ስለነበር ለውድድር ወደ አሜሪካ ሀገር ሄዱ። የሚሮጡበት ቦታ ዳገት ስለነበር ውድድሩን 11ኛ ሆነው አጠናቀቁ።

ከወድድሩ ከተመለሱ በኋላ የደመወዝ ክፍያው ተመልሶ ባለመጀመሩ እራሳቸውን ማስተዳደር ከበዳቸው። ምንም እንኳን ከነበሩበት ዝና ተመልሰው ወደ ቀያቸው ገብተው እርሻ ማረሱ ሲያስቡት ቢከብዳቸውም፤ አማራጭ ስላልነበራቸው ተመልሰው ማረስ ጀመሩ። ለስድስት ወራት እያረሱ ከቆዩ በኋላ፤ ሌሎች አትሌቶች ልምምድ እያደረጉ ነው ተብሎ ተነገራቸው።

ያለደመወዝ እንዴት እሠራለሁ የሚል ጥያቄ ቢፈጠርባቸውም፤ ለአትሌቲክስ ከነበራቸው ፍቅር የተነሳ ጨክነው መቅረት አልቻሉ። ገጠር የነበሯቸውን ከብቶች ሸጠው ተመልሰው መጥተው ዘመድ ቤት በማረፍ፣ በእጃቸው ያለችውን ገንዘብ ቆጥበው እየተጠቀሙ ወደ ልምምድ ገቡ።

"ከዛ ስመለስ ወደ አየር ኃይል ተዛውረሃል፤ ደመወዝ ይከፈልኃል ተባልኩኝ። ተስማምቼ ገባሁ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም ለአንድ ዓመት ሳይከፈለኝ የቆየ ደመወዜ እንዲከፈለኝ ከሌሎች አትሌቶች ጋር ጥያቄ አቀረብን። ጥያቄ ያቀረብንላቸው ባለሥልጣን ለምን እንዳልተከፈለን የሚመለከታቸው አካላት ሲጠይቁ ኢሠፓ ናቸው ብለው ፈረጁን።" ሲሉ ያስረዳሉ

በዚህ ምክንያት ከዛ ቀደም ለአንድ ዓመት የቀረውን ክፍያ ሳይሰጣቸው ቀረ፤ ምንም ማድረግ ስላልቻሉ የቀድሞ ክፍያቸው ቀረ። ተመልሰው ከገቡ በኋላ አየር ኃይልን ወክለው በአበበ ቢቂላ ውድድር መሳተፍ ቻሉ። ውድድሩ ላይ በአንደኝነት ከማሸነፋቸውም በተጨማሪም ውድድሩን በተሻለ ሰዓት አጠናቀቁ። ቀጥለው ወደ ዩጎዝላቪያ ሄደው ተወዳድረው ከመጡ በኋላ፤ በአትላንታ ኦሎምፒክ ለመሳተፍ ልምምድ ላይ እያሉ እግራቸው ላይ ቡጉንጅ ወጣ።

በዚህ ጊዜ ከአትሌቲክስ ተቆራርጠው እንዲቀሩ የሚያደርጋቸው ችግር አጋጠማቸው። እግራቸው ላይ የወጣውን ቡጉንጅ ለመታከም ወደ ፌደሬሽኑ ሐኪም ቤት ሄዱ። መዳንን ፈልገው ቢሄዱም ያልጠበቁት እና እቤት የሚያስቀራቸውን አደጋ አጋጠማቸው። ሐኪሙ መርፌ ሲወጋቸው ነርቫቸውን ስለነካ እራሳቸውን ያወቁት ዘውዲቱ ሆስፒታል ከደረሱ በኋላ ነው።

የተለያዩ ሕክምናዎችን ቢወስዱም ከሕመማቸው መዳን ከባድ ሆነ። ያጋጠማቸው ችግር የባሰ ጭንቀት ስላስከተለባቸው የመዳን ተስፋቸውን አዳጋች አደረገው። ቦርድ እንዲወጡ ከሐኪም ቤት ማስረጃ በማጻፍ ሄደው አመለከቱ። መውጣት እንደማይቻል እና ሐረር ሄደው በውትድርና እንዲሠሩ ነገሯቸው፤ በሕመም ምክንያት አልችልም በማለታቸው፤ ደመወዛቸው እንዲቋረጥ ተደረገ።

ለ21 ዓመታት በውትድርና ያገለገሉ ቢሆንም፤ የጡረታ መብታቸውም ሳይከበር ቀረ። በተለያዩ ስብሰባዎች ለሀገር መታገላቸውን እና የሀገርን ባንዲራ በዓለም ከፍ ማድረጋቸውን አንስተው ‹‹አሁን የተጣልኩበት መንገድ ተገቢ አይደለም።›› ብለው ስሞታ ቢያሰሙም ሰሚ ማግኘት አልቻሉም።

ከውትድርና እና ከአትሌቲክስ ሕይወት በዛ መንገድ



ፎቶ ኢዮብ ተፈራ

ከወጡ በኋላ በሌሎች ሥራዎች ለመቀጠር ቢሞክሩም የደርግ ወታደር ተብለው መገለል እንደደረሰባቸው የሚያነሱት አትሌት ፀጋዬ፤ "አንድ ጊዜ ግብርና ሚኒስቴር በዘበኝነት ተቀጥሬ ለመሥራት ተወዳድሬ ሁሉን ነገር ካጠናቀቁ በኋላ፤ የደርግ ወታደር እንደነበርኩ ሲያውቁ ሌላ ቀን እንጠራሃለን ብለው መለሱኝ፤ ተመልሰውም ሳይጠሩኝ ቀሩ።" ይላሉ።

"ከዛ በኋላ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ መኖሪያ ቤት ሰጥቶኝ ሲኒማ ቤቱ እንድሠራ ወሰደኝ። በአትሌቲክስ የሀገር ባንዲራ በዓለም ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ማድረጌን ተናግሮ ሠራተኞቹ እንዲያከብሩኝ ነገራቸውና መሥራት ጀመርኩ። በዚህም አትሌት ኃይሌ ባለውለታዬ ነው።" ሲሉ ይናገራሉ

"እዛ ለሦስት ዓመት ከሠራሁ በኋላ እዛ ከሚሠሩት ሠራተኞች አንዳንዶች እያጭበረበሩ እንደሆነ በማጋለጤ፤ የኔ መኖር ለስርቆት አመቺ ስላልሆነላቸው ሌላ ቦታ ተዛውሬ እንድሠራ ነገሩኝ። ምንም ባልሠራሁት ጥፋት ሊያዛውሩኝ ስለፈለጉ ተናድጄ ሥራውን ለቅቄ ወጣሁ። ኃይሌ እንድመለስ ሰው ልኮ ቢለምነኝም መመለስ ስላልፈለኩ ቀረሁ። ሰዎቹም አንዳንዶቹ ታሰሩ፤ ሌሎቹ ከሥራ እንዲለቁ ተደረገ። "ይላሉ።

አትሌት ፀጋዬ፤ የሁለት ልጆች አባት ናቸው። እርሳቸው ወደ ጦርነት ሲዘምቱ የመጀመሪያ ሚስታቸው ነፍሰጡር ነበረች። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ወደ ቤታቸው ተመልሰው እስከሚያውቁ ድረስ፤ የወንድ ልጅ አባት መሆናቸውን አያውቁም ነበር። ከመጀመሪያ ትዳራቸው ልጅ ቢያፈሩም ትዳራቸው ተመልሶ ሊቆም አልቻለም። ከጊዜ በኋላ ሌላ ሚስት አግብተው አንድ ሴት ልጅ ወልደዋል።

አሁን ላይ አትሌት ፀጋዬ እንደ ዕድል ከቀናቸው ሰዎችን ወክለው ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነው ይሠራሉ። ከዛ በተረፈ የመጀመሪያ ልጃቸው፣ አሜሪካ የምትኖር የአክስታቸው ልጅ እና አንዳንድ ጓደኞቻቸው እየረዷቸው በአዲስ አበባ ከተማ ይኖራሉ።

ለሀገራችን እና ለሕዝባችን ሠላም ይስጠን የሚሉት አትሌቱ፣ ሻለቃ ራህማቶ ሸባህ፣ አትሌት ደራርቱ ቱሉ፣ አትሌት ጌጤ ዋሚ፣ ሻምበል መገርሳ በተለያዩ ጊዜያት ላደረጉላቸው ድጋፍ አመስግነዋል። በተጨማሪም ለቀድሞ አትሌቶች በሙሉ ምስጋናቸውን ገልጸዋል።

"አትሌቱ መንገድ ስተው ከሄዱ በኋላ ተመልሰው በማሸነፋቸው አበረታች መድኃኒት ወስደዋል በሚል ጥርጣሬ ውድድሩን እንዳሸነፉ፤ ምርመራ ተደርጎላቸው አለመውሰዳቸው ተረጋግጦ ሽልማታቸውን ለመውሰድ ችለዋል። በውድድሩ ኢትዮጵያ ሁለት ወርቅ ስታገኝ አንዱን ያስገኙት እኚሁ አትሌት ናቸው።"

# ባህልና ቱሪዝም

# ወራትን የተሻገረ ሙሽርነት በጋሞ ዱቡሻ ሶፌ ባሕላዊ ሥርዓት

በመቅደስ ታዬ (ፒ ኤች ዲ)

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀገራት ለሀገር በቀል እውቀት፣ ባሕል፣ እና ማንነት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ለአንድ ሀገር ዘለቄታዊ እድገት እና የተሻለ ሽግግር አዋጪ ሆኖ የተገኘው ከራስ ማንነት እና ልምምድ ላይ የተነሳ፣ እሱንም ያከበረ እና ያካተተ ዘመናዊነት ነው ሲሉ ምሑራን /ለምሳሌ አኬ (1994)፣ ሀውንቶንዲ (2000)/ ያመለክታሉ። በዚህም አግባብ የራስን ማንነት፣ ባሕል እና ሥርዓት በልኩ የተረዳ ትውልድ ይህ እውነታ ነገን ለመሥራት ስንቅ ይሆንለታል የሚል ድምዳሜን ያክላሉ።

በሀገራችን በርካታ ወጎች፣ የአኗኗር ስልቶች፣ የአመራር እና አስተዳደር ልዩ ጥበቦች በአጠቃላይ በርካታ ባሕሎች ከነአስገራሚ ክንውኖቻቸው በኅብር ይኖራሉ። ከእነዚህ ልዩ ማንነቶች ውስጥ የጋሞ ብሔረሰብ ማንነትን የሚገልጹት ባሕሎች ይጠቀሳሉ። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዚህ ብሔረሰብ ስም እኩል በሚባል ደረጃ የሚነሳበት ትልቅ አሻራ ያስቀመጠ ተግባር አለ። ይህም የጋሞ አባቶች ልዩ ግጭትን የማብረድ እና የመፍታት ችሎታ እና ጥበብ ነው።

በመከባበር እና በእውነተኝነት ላይ ጥብቅ አቋም ያለው የጋሞ ባሕል በማኅበረሰቡ ዘንድ ልዩ ቅቡልነት ስላለው በቃል ብቻ እየተላለፈ ዘመናትን ተሻግሮ እስከ ዛሬ የዘለቀ በፍቅር እና በእኩልነት ማኅበረሰቡን እያስተዳደረ የሚገኝ ባሕላዊ ሥርዓት አለው። እኛም በቦታው ተገኝተን ይሄን እና ሌሎች አስገራሚ ኩነቶችን ታድመን አስፈላጊ መረጃዎችንም ሰብስበን እንደየይዘታቸው ከፋፍለን ለአንባቢያን ማድረሳችንን ቀጥለናል። ለዛሬ ልናካፍላችሁ የወደድነው በብሔሩ የመስቀል በዓልን ተከትለው ከሚከወኑ አስደሳች እና ተናፋቂ ድርጊቶች መካከል አንዱ ስለሆነው የሶፌ ሥርዓት ነው።

በጋሞ ብሔረሰብ መስቀል ከሌሎች ሃይማኖታዊ በዓላት በተለየ በልዩ ክብር እና ዝግጅት ከሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በአንድነት እና በጉጉት ተናፍቆ የሚከበር በዓል ነው። አስደማሚ ባሕላዊ ክዋኔዎች ቀኑ ከመድረሱ ቀደም ብለው ሲተገበሩ ይቆዩ እና ዝግጅቶች በዋናነት በዋዜማው ማለትም በመስከረም 16 መከወን ይጀምራሉ። ይሄንኑ ኩነት ለመታደም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በዞኑ ኮሙኒኬሽን ኃላፊ እየተመራ ባሕሉን ከምንጩ ለማየት በዶርዜ ቀበሌ ተገኝቷል። በዚህ ቀበሌ የተካሄዱትን ባሕላዊ ድርጊቶች እንዳጠናቀቀም የሶፌ ሥርዓት ወደሚካሔድበት ድቡሻ አቅንቷል።

የጋሞ ብሔረሰብ እርቁን፣ እቅዱን፣ መረጃ ልውውጡን በአጠቃላይ ባሕሉን እና ዋና ዋና የማኅበረሰቡን ጉዳዮች የሚከወንበት ቦታ ድቡሻ ይባላል። በዚህ ድቡሻ ላይ ጥንዶች አምረው ተውበው በባሕላዊ አልባሳት ደምቀው በተጠቀሰው ቀን ይወጣሉ፤ እኛም በስፍራው ጥንዶቹን የመመልከት ዕድሉን አግኝተናል። ጥንዶችን ካየን በኋላ ስለጉዳዩ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት የአካባቢውን ሽማግሌዎች፣ ምሑራን እና በባሕሉ ላይ ጥናት እና ምርምር እያከናወኑ ያሉ አካላትን አነጋገርን።

በጋሞ ማኅበረሰብ አንድ ሴት ባፈራት ቤተሰብ፣ በመልኳ፣ በግብሯ እና በቁም ነገሯ ተመርጣ ትታጫለች። የ ስምንት ደሬዎች አስተዳዳሪ የሆኑት ካዎ ታደሰ በተለይ ከ ዘ ኢትዮጵያን ሄራልድ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለፁት፤ ለጋብቻ የተመረጠችው ሴት በባሕሉ መሠረት ሽማግሌ ተልኮ ከብዙ ምልልስ በኋላ ፈቃድ ከተገኘ ጋብቻው ይከናወናል።

ጋብቻ በሌላ መልክም ሊፈፀም ይችላል። ካዎ ታደሰ እንዳብራሩት፤ ጠለፋም አንዱ የጋብቻ አይነት ነው። ወንዱ እና ሴቷ ከተስማሙ ሴቷ በፈቃደኝነት እንዲጠልፋት ሁኔታዎችን ታመቻቻለች። ከዛ



ፎቶ፡ ሐዲስ አብርሃ

እሱም ጓደኞቹን እና የጎሳውን ሰዎች አስተባብሮ ይጠልፋታል። በዚህ ሰዓት ቤተሰቦቿ እና ዘመዶቿ ፈጥነው ሳይወስዷት ቀርተው የልጁ ቤተሰቦች ባዘጋጁላት ጫጉላ ቤት ከገባች ቤተሰቦቿ የግድ ለጋብቻው ይስማማሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት የጋብቻ አይነቶች በአንዱ ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ ሙሽሪት የምትሄደው የባሏ አባት በጊቢው ውስጥ ወደ ሠራላቸው መኖሪያ ቤት ነው። በዚህ ቤት ውስጥ ሙሽሪት ምንም አይነት የቤት ሥራ እንድትሠራ አይጠበቅም፤ ከቤት እንድትወጣም አይፈቀድም።

የጋሞ ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አዲሱ አዳሙ (ፒ ኤች ዲ) በጉዳዩ ላይ እንደተናገሩትም፤ መስቀል ከመድረሱ በፊት ዓመቱን በሙሉ የተፈፀሙ ጋብቻዎች የሚመረቁት እና እውቅና ከማኅበረሰቡ የሚያገኙት በዳመራ እለት ስለሆነ ያገቡ ሴቶች ከቤታቸው ሳይወጡ በባላቸው እናት እና እህት በምግብና በመሳሰሉት እንክብካቤ እየተደረገላቸው፣ እየተዋቡ፣ በከፍተኛ እንክብካቤ በቤታቸው ይቆያሉ።

ለምሳሌ ባነሳነው ጉዳይ ላይ ሙሽራዋን በመንከባከብ እና በመመገብ ሂደት ውስጥ የባልዬው እናት ትልቅ ሚና አላት። ምግብ አጣፍጣ በልዩ ሁኔታ ታቀርብላታለች። አቶ አዲሱ እንዳብራሩት፤ ምግቡ ውስጥ የሚጨመረውን ጨው እንኳን መቅመስ አይፈቀድላትም። የዚህ አመክንዮ ምግቡ ጣፍጧት እንዳትጓጓ ታስቦ ስልሆነ መቅመስ ጎሜ ነው ተብሎ ይታሰባል።

አቶ አዲሱ አያይዘው እንደገለጹት፤ በጋሞ ባሕል እንደ ኃጢያት ወይም እንደ እርግማን የሚቆጠሩ ድርጊቶች ጎሜ ይባላሉ። ስለዚህ ባሕሉ የማይፈቅደውን መፈፀም ኃጢያት ስለሚሆን ማኅበረሰቡ እነዚህን ኃጢያት የሚያስብሉ ጉዳዮች ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ሥርዓታቸውን ሳያጓድል ይፈፅማል።

የባልዬው እናት ሙሽራዋን ማየትም አይፈቀድላትም። እሳቤው የመጣው የሙሽራዋን ሰውነት አይታ ትገመግማታለች ፤ በዚህም ሙሽራዋ ልትሳቀቅ ትችላለች ተብሎ መሆኑን አቶ አዲሱ ነግረውናል። አማቷ ካየቻት ግን ጎሜ ወይም ኃጢያት ሠራች ይባላል። ስለዚህ ሰውነቷን ሳታይ ምግቡን ብቻ እያጣፈጠች ታቀርባለች።

በዚህ እንክብካቤ ውስጥ ሙሽሪት ከወራት ያለፉ ምቹ ጊዜያትን ታሳልፋለች። በዚህ መካከል ልጅ የምትወልድ ከሆነ ከጫጉላው ትወጣና እንደማንኛውም ሰው ትዳሯን መምራት ትጀምራለች። ያነጋገርናቸው ሽማግሌዎች እንደገለፁት፤ ልጅ ከተወለደ ጋብቻው በራሱ ጊዜ በማኅበረሰቡ እውቅና ያገኛል። ይህም ማለት ወደ አደባባዩ ወይም ድቡሻው መምጣት አያስፈልግም ማለት ነው።

ሶፌ ማለት በዓመቱ ጋብቻ የፈፀሙ ጥንዶች ለእውቅና ወደ ድቡሻ መምጣት ማለት ነው። ይህን የሶፌ ፕሮግራም ለማካሄድ ሲባል ጋብቻዎች ከሚያዚያ ወር በኋላ እንዲፈፅሙ ይመከራሉ። ያ ማለት በሚያዚያ ከተፈፀመ እስከ ዳመራ በዓል ድረስ የሚኖረው ጊዜ አምስት ወር ብቻ ስለሚሆን መውለድ አይኖርም ማለት ነው። ስለዚህ ጥንዶቹ በአደባባዩ እንዲገኙ የሚጠበቀው ልጅ ሳይወልዱ ነው።

ስለዚህ አምስት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ወራት በእንክብካቤ እና በምቾት የቆየችው ሙሽራ በዳመራ እለት እጅግ ተውባ፣ እንደ የቤተሰቡ አቅም እና ደረጃ በአልባሳት ደምቃ ትወጣለች። እዚህ ላይ ከአልባሳቱ በተጨማሪ የሚፈፀም አስገራሚ ጉዳይ አለ። ወደ ድቡሻው የምትወጣው ሙሽራ መጠኑ ከፍ ያለ ምንአልባትም ከአንድ ኪሎ በላይ የሚሆን የፀጉር ቂቤ ጭንቅላቷ ላይ ታስቀምጣለች። ቂቤው ወደላይ በጥንቃቄ ተደራረቦ ከተቀመጠ በኋላ በቀጭን ጨርቅ ወደ ግምባሯ እንዳይፈስ ይታሰራል። ጉዳዩ በዚህ አያበቃም።

በጭንቅላቷ ዳር ለዳር ዙሪያውን የሰጎን ላባ በምትችለው ልክ እንደ ቤተሰቡ ጉብዝና ትሰካለች። የላቫው ብዛት ለሚሰጣት ክብር እና እውቅና ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው በፕሮግራሙ ላይ የተሳተፉ ምሑራን ነግረውናል።

ትኩረታችንን የሳበውን የቂቤ ብዛት ትርጓሜ ደግሞ ጠየቅን። አቶ አዲሱ ሲመልሱልን፣ የቂቤው ብዛት የባሏን ቤተሰቦች የሀብት መጠን፣ የልግስና ገደብ፣ ደግነታቸውን እና የጎሣቸውንም ደረጃ እና መልካምነት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። የሰጎን ላቫው ብዛትም የቤተሰቦችን ጉብዝና ያሳያል፣ ምክንያቱም ሰጎን በቀላሉ ስለማይገኝ ላባው በበዛ ቁጥር ጉብዝናቸውም ከፍ ያለ እንደሆነ ያሳያል ሲሉ አብራሩልን።

ሙሽሮቹ ከተጠቀሱት ነገሮች በላይ የበዙ ጌጣጌጦች እና አለባበሶችንም በተለያየ መልክ ያደረጉ ሲሆን፣ የተወሰኑት ቡሉኮ ለብሰዋል። ቡሉኮ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ እጅግ የተከበረ እና የተወደደ ፍቅርን እና አክብሮትን ለማሳየት የሚጠቀሙበት በብሔረሰቡ የሚሠራ ባሕላዊ ልብስ ነው።

እነዚህ ጥንዶች በቤተሰቦቻቸው፣ በአካባቢው ሰዎች ዳንኪራ እና በከፍተኛ አጀብ ወደ ድቡሻው ይመጣሉ። በዚህ ሰዓት የአካባቢው ሰዎች በተለይ ሙሽራዋን ለማየት የሰውነቷን መመቸት እና መጎሳቆል ለማጣራት እና ለመፍረድ ይሰበሰባሉ። ጥንዶቹ በድቡሻው ውስጥ ከገቡ በኋላ ከፍ ወዳለ ቦታ ይወጣሉ። ይህም እንደ መድረክ ስለሚያገለግል የተሰበሰበው ሕዝብ ጥንዶቹን ለማየት እንደመቸው ታስቦ የሚከወን ባሕል ነው።

ጥንዶቹ በምስሉ ላይ በሚታየው መልክ ይደረደራሉ። እንደ ቁንጅና ውድድርም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሶፌን ግን ለየት የሚያደርገው ሙሽራዋ በሰውነቷ ምቾት፣ ማማር እና ውፍረትም እንድትመዘን ያዛል። ይሄን ውድድር የሚዳኙ ሽማግሌዎች ተመርጠው ቦታቸውን በመያዝ ዳኝነቱን ይፈፅማሉ። ውጤቱም በሕዝብ ፊት ተገልፆ ውሳኔው ይፀድቃል።

በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ውድድሩን ያሸነፉ ጥንዶች ምርቃት እና እውቅና ይሰጣቸዋል። ከምንም በላይ የአሸናፊ ቤተሰቦች በማኅበረሰቡ ውስጥ ትልቅ አድናቆት፣ ክብር፣ ፍቅር ያላቸው እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ተደርገው ይወሰዳሉ። በውድድሩ ተጎሳቁላ እና ተጎድታ የታየችን ሴት ቤተሰቦች ሕዝቡ አይቶ አዝኖ ይገስፃል። በአጠቃላይ ግን በእለቱ ለሶፌ ፕሮግራም የወጡ ጥንዶች በሕዝቡ ዘንድ እውቅና እና ክብር አግኝተው ተመርቀው ከዚያች ቀን በኋላ በይፋ በነፃነት ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው መኖር ይጀምራሉ። እስከዚች ቀን ግን በፍፁም በተለይ ሴቷን ሰው እንዲያያት አይፈቀድም።

ይህን ሥርዓት ካዎ ታደሰ እንደገለፁት፤ እጅግ በጣም አስፈላጊ እና መበረታታት ያለበት ነው። ለባሕሉ ሲባል ሙሽሪቷ በዚያ ልክ የባሏ ቤተሰቦች እንዲንከባከቧት መደረጉ በዋናነት ልጅቷ ከቤተሰቦቿ እንደመምጣቷ ቤቱን እና ኑሮውን እስክትጀምር ጥሩ መለማመጃ ጊዜ ይፈጥርላታል። ከዚህ በተጨማሪ ከባለቤቷ ቤተሰቦች ጋር ለሚኖራት ረጅም ቆይታ ሶፌ ጥሩ መግባቢያ መንገድ ይሆንላታል። የባሏ ቤተሰቦች ሲንከባከቧት ደግነታቸውን፣ ሙያቸውን፣ ሥነሥርዓታቸውን አጠቃላይ ባሕሪያቸውን ትረዳለች። ይህም በቀጣይ ለሚኖራት መልካም ግንኙነት ትልቅ ዐሻራ ያስቀምጣል። የቤተሰብ ሠላም እና መረጋጋት የማኅበረሰብ ግምባታ መሠረት ስለሆነ። ይሄን ቀናነት እና ፍቅር ያገኘች በተግባር የተለማመደች ሴት ነገ የምትፈጥረው ቤተሰብ በዚህ የተገራ ነው ብንል ምክንያታዊ ነው።

በጋሞ ብሔረሰብ ሴት ልጅ ከሙሽርነቷ ጊዜም ባሻገር ግጭትን በመፍታት ሂደት ውስጥም ትልቅ ድርሻ አላት። በእዚህ አካባቢ ያገኘናቸው ሀለቃ እንደተናገሩት፤ ግጭት ሲፈጠር፣ ወጣቶች ወደ አላስፈላጊ መስመር ሲገቡ እንድ እናት ተንበርክካ ከለመነች ግጭቱ ወዲያው ይቆማል። እናት ክብር እናት አዛኝ እናት፤ ልጆቿን አጥብታ የምታሳድግ ስለሆነች በማኅበረሰቡ ዘንድ ትከበራለች። ወጣቶች የእሷን ልመና ትተው ከሄዱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ኃጢያት ወይም ጎሜ ይሆናል።

የጋሞ ድቡሻ ሶፌ ሥነ-ሥርዓት በዚህ ጽሑፍ ከተገለፀው በላይ ጥልቅ ትርጓሜ እና ድንቅ ሀገር በቀል እውቀት የታጨቀበት፣ የማኅበረሰቡን አርቆ አሳቢነት፣ ትንበያ፣ ለአብሮነት የሚከፈልን ቀላል የሚመስል ነገር ግን ትልቅ መሠረት የሚጥልን ልምድ እያሳየ ያለ ባሕል ነው ብንል መነሻችን አባባላችንን ይደግፈዋል።

ምንም እንኳን ዞኑ ባሕሉን ለማስተዋወቅ እና ለመጠበቅ እየሠራ መሆኑን ቢጠቅስልንም፣ ባሕሉ ሊሰጥ ከሚችለው ጥቅም እና ፋይዳ አንፃር ይህ ሥራ በተወሰነ ባለድርሻ አካል ብቻ መወሰን አለበት ብለን አናምንም። እንደዚህ ያሉ ሀገር በቀል እውቀቶች እና ልምምዶች እያሉ፣ የተሻለ ነገር የሌላቸው የሌሎች ሀገሮችን ፍልስፍና መከተል አይገባም፤ ይህን በሚገባ በመገንዘብ ወደ ራስ ማንነት መመለስ ለውጤታማነት ያስፈልጋል።

ስለዚህ ሁሉም ዜጋ በኃላፊነት ራሱን ማወቅ እና በማንነቱ መኩራት እንዲሁም መጠበቅ አለበት። ይህን ማንነት ማሻሻል አያስፈልግም፤ በእውቀት ላይ ተመሥርቶ ማድረግ ከቻለ ሀገራችን ያሏት ባሕሎች በቂ የመፍትሔ ቋቶች ናቸው ብለን እናምናለን። እኛም እንደሚዲያ የሚጠበቅብንን የማስተዋወቅ ሥራ አጠናክረን እንቀጥላለን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# ንጉሠ የንጉሥ አባት

ዋስልኝ አየለ



ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴ

የልጅየው ታሪክ በለጠና የአባትየው ታሪክ የተዋጠ ይመስላል። እኚህ ሰው የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ አባት የሸዋው ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለ ሥላሴ ናቸው። ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ጋር ጦርነት ሊገጥሙ በአንኮበር ቆራ መስክ ላይ ዝግጅት እያደረጉ ከ169 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 30 ቀን 1848 ዓ.ም ያረፉት ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው የዚህ ሳምንት ክስተት የሆኑ ሌሎች ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ታሪኮችን እናስታውስ።

ከ24 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 26 ቀን 1993 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ፣ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው በክብር ተፈጸመ። ነሐሴ 20 ቀን 1967 ዓ.ም ሕይወታቸው ያለፈው ንጉሠ ነገሥቱ የሞቱበት ምክንያት አሁንም ድረስ አከራካሪነቱ ቀጥሏል። በደርግ በኩል ታመው እንደሞቱ ሲነገር፤ ደርግን አናምነውም የሚሉ ወገኖች ደግሞ ራሱ እንደገደላቸው ይገምታሉ። ደርግን አስወግዶ ሥልጣን የያዘው ኢሕአዴግ ጥቅምት 26 ቀን 1993 ዓ.ም የክብር ሥርዓተ ቀብራቸውን አስፈጽሟል።

ከ12 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም ስመ ጥሩውና አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ አረፈ።

‹‹... ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ ገብሬ! ገብሬ የመታውን የዚምባብዌው 2 ቁጥር በራሱ ግብ ላይ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ... ››

‹‹ ... አሁን ዳኛቸው ነው የሚመታው ... አሁን ዳኙ ሊመታ ነው ... አሁን ይገላግለናል ... ወይኔ! ወይኔ ዳኙ! ዳኙ አገባ! ዳኘሻ አገባ! በጣም አስደናቂ ግብ ነው ዳኘሻ! ቀኙን አሳይቶ ግራውን፤ ግራውን አሳይቶ በቀኙ ... አሁን ተጨዋቾቻችን ደስታቸውን እየገለጹ ነው! ... ሕዝቡ ወደ ሜዳ እየገባ ነው ... ተመልካቹም ‹እንደተመኘኋት አገኘኋት› እያለ ነው ... ችቦ በራ! ስታዲየሙ ተንቀለቀለ...›› ደምሴ ዳምጤ በዚህ የደስታ ሲቃ ድምፁ በብዙዎች ዘንድ ይታወሳል።

ከ135 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ አስተዳደር መቃናትና ስኬት ትልቅ ድርሻ የነበራቸው ባለቤታቸው ጣይቱ ብጡል ‹‹እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ›› ተብለው፣ ምኒልክ በነገሡ በሦስተኛው ቀን፣ የእቴጌነት ዘውድ ደፉ። እነሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ‹‹እቴጌ ጣይቱ›› በመባል ይታወቃሉ።

ከ88 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 27 ቀን 1929 ዓ.ም ስመ ጥሩው አርበኛ፣ የጦር መሪና ግዛት አስተዳዳሪ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ) አረፉ።

**ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ**
**መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ**

የሚለው ስንኝ ዓድዋ በመጣ ቁጥር የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ማድመቂያ ነው፤ የጋዜጣና መጽሔቶች ጽሑፍ መግቢያ ነው። ይህኛው ነጥሮ የወጣ የባልቻ አባ ነፍሶ ውዳሴ ይሁን እንጂ ሌሎች ስንኞችም አሉ።

**እንደ ደጋ ገብስ እንዲያ ኮስሶ**
**ያስቆረጥማል ጠላቱን ኮሶ**
**የዳኘው ጀግና ባልቻ አባ ነፍሶ**
**ማን እንዳንተ አርጎታል የእርሳሱን ጉትቻ**
**የዳኘው አሽከር አባ ነፍሶ ባልቻ!**

ስለባልቻ አባ ነፍሶ ብዙ ተዘምሯል። ይቺኛዋን ግን እናስታውስ፤ የዓድዋው ጦርነት ስመ ጥሩ ጀግናው ባልቻ አባ ነፍሶ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያ በድጋሚ ስትወረር ከቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ጋር ፀብ ስለነበራቸው ባልቻ ከጣሊያን ጎን ይሰለፋሉ ብለው ጣሊያኖች አስበው ነበር። ደጃዝማች ባልቻ በንጉሡ ላይ ቅሬታ ቢኖራቸውም በሀገር ጉዳይ ላይ በፍፁም ሌላ ድርድር ውስጥ መግባት አልፈለጉም። ጦራቸውን ማሰባሰብ ጀመሩ እናም ከነ ደጃዝማች ኃይለማርያም ማሞ፣ አበበ አረጋይ፣ በላይ ዘለቀና አቡነ ጴጥሮስ ጋራ ስለ ጦርነቱ የምስጢር ደብዳቤ መለዋወጥ ጀመሩ። ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ አምስት ሺህ ጦራቸውን ይዘው ከትውልድ መንደራቸው ከአገምጃ ሶዶ ተነስተው አዲስ አበባ ደረሱ፤ ከዚያምም ረጲ ተራራ ላይ ሆነው መድፋቸውን ጠምደው የሌሎችን አርበኞች መልዕክት ይጠባበቁ ጀመር። ሺህ የባልቻ ሰላይ የነበሩት በባንዳ ተይዘው ሲገደሉ ጣሊያን በአውሮፕላን ሆኖ የደጃዝማች ባልቻ ጦርን እየተከተለ ብዙ ጉዳት ቢያደርስባቸውም በከፍተኛ የሀገር ፍቅር ወኔ የሠሩት ሥራ ፍሬ አፍርቶ የሀገራቸውን ነፃነት አስጠብቋል። እርሳቸውም ይሄው በጀግንነት ይታወሳሉ።

ከ55 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 27 ቀን 1962 ዓ.ም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ተመርቆ ተከፈተ። ፋብሪካው የተገነባው በኢትዮጵያ እና በኔዘርላንድስ መንግሥታት ትብብር ነበር።

ከ35 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 30 ቀን 1982 ዓ.ም (ኖቬምበር 9, 1989) በርሊንን ‹ምሥራቅ› እና ‹ምዕራብ› አድርጎ ከፍሏት (ለያይቷት) የነበረው ‹‹የበርሊን ግንብ›› ፈረሰ። ሁለቱን ጀርመኖች ከማዋሓዱም ባሻገር የኮሚኒዝም ሥርዓትን ያፈረሰ ነው ተብሎ ይነገርለታል።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴ ታሪክ እንለፍ።

የታሪክ ፀሐፊው ፍስሐ ያዜ ‹‹የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢሕአዴግ›› በሚለው ቅጽ 1 መጽሐፉ በ81ኛው ምዕራፍ ላይ እንዲህ ይለናል።

‹‹... ልጅ ምኒልክ የአፄ ልብነ ድንግል ልጅ ከሆኑት ከአፄ ያዕቆብ ትውልድ 13ኛ የዘር ሐረግ ላይ ይቀመጣሉ። አያታቸው ሣሕለሥላሴ የሸዋውን ንጉሥ ኃይለመለኮትን ይወልዳሉ.....›› እያለ ይቀጥላል። ስለዚህ ንጉሥ ኃይለመለኮት ከአፄ ልብነ ድንግል ዘር 12ኛ የዘር ሐረግ ላይ ይቀመጣሉ።

ንጉሥ ሣህለሥላሴ (የንጉሥ ኃይለመለኮት አባት) ለ33 ዓመታት ከ 5 ወራት ያህል ሸዋንና በሸዋ ዙሪያ ያለውን ቦታ ሲያስተዳድሩ ቆይተው ጥቅምት 12 ቀን 1840 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ፣ ዙፋኑን የወረሱት ልጃቸው ንጉሥ ኃይለመለኮት ናቸው።

ንጉሥ ኃይለመለኮት በሰውነታቸው ግዝፈትና ጥንካሬ እንዲሁም በልባቸው ቀናነት በሸዋ ዘንድ የታወቁና የተወደዱ ንጉሥ ነበሩ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ›› በሚለው መጽሐፋቸው እንደሚነግሩን፤ ንጉሥ ኃይለመለኮት ከጥንካሬያቸው የተነሳ ዒላማ ተኩስ በሚተኩሱ ጊዜ መሣሪያውን አጠንክረው በመያዛቸው ምክንያት ጥይቱ ሲወጣ ጠመንጃቸው ለሁለት ተሰብሮ እጃቸው ላይ ቀርቶ ያውቃል።

ንጉሥ ኃይለመለኮት ሸዋን ለ8 ዓመታት ያህል አስተዳድረዋል። በሥልጣን ላይ ሳሉም ተቀናቃኝ ሊሆኑባቸው የሚችሉትን ወገኖቻቸውን እንዲያስሯቸውና እንዲያስወግዷቸው ሰዎች ሲመክሯቸው፣ ‹‹ተዉ! ይሄን አላደርገውም! እግዚአብሔር የወደደውን ነው የሚያነግሠውና የሚያስገዛው›› የሚሉ ቀና ሰው እንደነበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በመጽሐፋቸው ጠቅሰውታል።

የጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ካሣ ኃይሉ የዘመነ መሳፍንትን የየአካባቢ መስፍኖች ሁሉ አሸንፈው፣ ‹‹ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ›› ሆነው ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ታዲያ ራስ ዓሊ ተቀናቃኛቸው ነበሩ። የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኝ የሆኑት ራስ ዓሊ የሸዋ ንጉሥ በነበሩት በንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴ እየተደገፉ አልያዝ አሉ። ይህ ሲሆን ሸዋ ለአፄ ቴዎድሮስ እየገበረ አልነበረም። አፄ ቴዎድሮስ በነገሱ በዓመቱ (በ1846 ዓ.ም ማለት ነው) ትግራይን እና ወሎን አስገብረው ሸዋ ገቡ።

አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን አስገብረው ግሼ ሲደርሱ የግሼው ሹም አቶ ሀብተማርያም ተዋግተዋቸው ነበር፤ ሆኖም ሀብተማርያም ድል ሆኑ። አፄ ቴዎድሮስ መንዝ ሲደርሱ የይፍራታና ግድም ሕዝብ መገበር ጀመረ። ጉር ሥላሴ ሲደርሱ ግን ብዙ ሕዝብ መዋጋት ጀምሮ ነበርና ንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ሰው አለቀባቸው። ይህ ከሆነ በኋላ ነው እንግዲህ የሸዋው ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለ ሥላሴ ከሚኖሩበት ከተማ አንኮበር ወጥተው ቆራ መስክ ላይ አፄ ቴዎድሮስን ለመዋጋት የተዘጋጁት። በመሐል ባሉ አካባቢዎች ውጊያዎች ሲደረጉ ቆይተው ንጉሠ ነገሥት አፄ ቴዎድሮስ እና ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴ ሳይገናኙ ኃይለመለኮት ያደረባቸው ሕመም ጠንክሮ ጥቅምት 30 ቀን 1848 ዓ.ም ሌሊት ማረፋቸው ተሰማ።

በዚሁ በጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ ላይ እንደተጻፈው፤ ንጉሥ ኃይለመለኮት የሞቱት ከአፄ ቴዎድሮስ በተላከ መልዕክተኛ ተመርዘው ነው የሚል ሐሜት ነበር። በአንኮበር የሚገኙ የውጭ አገር ሰዎች እንደጻፉት ግን ኃይለመለኮት የሞቱት በንዳድ (ወባ ማለት ነው) በሽታ ነው።

ከንጉሥ ኃይለመለኮት ሞት በኋላ የሸዋ ሰዎች ንጉሣቸውን ቀብረው፤ የ11 ዓመት ልጅ የሆነውን ምኒልክን (በኋላ አፄ ምኒልክ) ይዘው ሸሹ። ይህን የሰሙት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከደብረ በግዕ ተነስተው ጠራ ገቡ። ጠራን ካስደበደቡ በኋላ ምኒልክን እያባረሩ ወደ መገዘዝ እንደደረሱ ራስ እንግዳ የሚያዝዙትን ጦር ወደ በረኸት ሰደው አፄ ቴዎድሮስ ወደ ምንጃር ተሻገሩ። ሕጻኑን ምኒልክን ይዘው ይሸሹ የነበሩ የሸዋ ሰዎች ከአረርቲ ቆላ ቆላውን ሄደው፣ ከሰምን ተሻግረው፣ በረኸት ብቅ ሲሉ ከራስ እንግዳ ጦር ጋር ተጋጠሙ። በዚያ ቦታ ጦርነት ተደርጎ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ። ከምኒልክ ጋር ብዙ ሰዎችም አብረው ተሰደው ነበር። በዚያን ጊዜ በመኳንንቱ እንዲህ ተብሎ ተገጠመ።

**ቁርጡን አወቁና አለመኖርህን**
**በረኸት አገቡት ጌታዬ ልጅህን**

የዚህ ግጥም መልዕክት ለሟቹ ንጉሥ ኃይለመለኮት ሣሕለሥላሴ ይመስላል። የእርሳቸውን አለመኖር ልጃቸው ምኒልክ በስደት ተንከራተተ ማለት ነው።

ከጦርነቱ በኋላ የንጉሡ ልጅ የሆኑት ምኒልክ ተመለሱ። ምኒልክን ይዘው የሚሸሹት ሰዎች የአፄ ቴዎድሮስን ሠራዊት ብዛት፣ የጦርነቱንም ብርታት አይተው ነበርና ምንጃር ሆነው ሲማከሩ፤ ግማሾቹ ምኒልክን ይዘን ወደሌላ ቦታ እንሂድ ብለው ተማከሩ። ሌላው መካሪ ደግሞ ሕጻኑን ይዘን ሀገር ለሀገር ከመንከራተትና አፄ ቴዎድሮስም ተከታትለው ከሚወስዱብን በፈቃዳችን ብንሰጣቸው ይሻላል ብለው መከሩ። የጉባኤው ሀሳብ ለሁለት በመከፈሉ ምንም እንኳን ሕጻን ቢሆንም የምኒልክ ሀሳብ ይጠየቅ ተባለ። ሕጻኑ ምኒልክ ለአፄ ቴዎድሮስ ከሚሰጥ እና ወደ ሌላ ቦታ ከሚወሰድ ምርጫ ቀርቦለት ወደ ሌላ ቦታ መወሰድን መርጧል።

ይህ ሁሉ ሲሆን አፄ ቴዎድሮስ አንኮበር ነበሩ። አንኮበር ሆነውም ‹‹አባት ያለህ የአባትህን እሰጥሃለሁ መርቅ፤ አባት የሌለህ ግን አባትህ እኔ ነኝና ደጅ ጥናኝ›› የሚል አዋጅ ስላስነገሩ ብዙ የሸዋ ሰዎች የአባታቸውን ሀገርና ሹመት እናገኛለን በማለት ለአፄ ቴዎድሮስ መግባታቸው ተሰማ። ይህን ጊዜ አቶ አንዳርጋቸው የተባሉ ከምኒልክ ጋር ተሰደው የነበሩ ወደ ምኒልክ ጠጋ ብለው ‹‹ይህን የመሰለ አዋጅ ተነገረ፣ ንጉሡ ቃልኪዳናቸውን የማያፈርሱ ቆራቢ ናቸው፣ አቡነ ሰላማም ደግ ጳጳስ ናቸው ይባላልና የአባትህን አልጋ አይነጥቁህም›› በማለት ለምኒልክ አስረድተውና አግባብተው ወደ አፄ ቴዎድሮስ ይዘዋቸው ገቡ። ይህ የምኒልክ በአፄ ቴዎድሮስ መያዝ በታሪክ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ምኒልክ በአፄ ቴዎድሮስ ከተማረኩ በኋላ እንደ እስረኛ ሳይሆን እንደ ልጅ ተንከባክበው ይዘዋቸው እንደነበር በታሪክ ተጽፏል።

አፄ ምኒልክ ለዚህ ሁሉ የበቁት የንጉሥ ኃይለመለኮት ልጅ መሆናቸው ነው።

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የንጉሡን ልጅ ምኒልክን እንደ ልጃቸው ማየት ብቻ ሳይሆን፤ የንጉሥ ኃይለመለኮት ሞት አሳዝኗቸው ነበርና አስከሬናቸው እንደገና ወጥቶ በንጉሣዊ የቀብር ሥርዓት እንዲቀበሩ አድርገዋል። ከዚያ በኋላ ያለው ታሪክ የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ እና የንጉሥ ኃይለመለኮት ልጅ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ነው።

# የዝነኞች ገጽ

# ከታዳጊነት እስከ ጉልምስና በሙዚቃ ዝና

**ቤዛ እሸቱ**

እንደብዙዎቹ የሀገራችን ቀደምት ድምፃውያን ለሙዚቃ ስትል ከቤተሰብ አልተጣላችም። ሙዚቃ አሡናኝ ብላ የበርካቶችን ደጅ አልጠናችም። ሙዚቃ እራሷ ፈልጋት መንገድ ያበጀችላት ይመስላል። ውልደትና እድገቷ የጥበብ መናኸሪያ በሆነችው ሸሮሜዳ ነው። በመኖሪያ ቤታቸው ማንኛውንም ሥራ ስትሠራ ሙዚቃ እየሰማች አብራ ታንጎራጉራለች። በተለይ የብዙነሽ በቀለ፣ የንዋይ ደበበና የሐመልማል አባተ ሥራዎችን አብዝታ ትዘፍናለች። መጀመሪያ አካባቢ ቤት ውስጥ ስታዜም "እባክሽ አትረብሽን" የሚሉ ድምፆች ይሰሙ እንጂ ተቃውሞም ይሁን ማበረታቻዎች አልነበሩም።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በተከታተለችበት የአመሐ ደስታ የሙዚቃ ቡድን ቢኖርም ለመቀላቀል አላሰበችም። ግን ደግሞ የቅርብ ጓደኞቿ ስትዘፍን ድምጿን ሰምተው ተደንቀዋል። አንዲት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ መዝፈን ትችላለች የሚል ወሬ ቡድን መሪው ጋር ደርሷል። በኃይለኝነቱ የሚታወቀው ይህ ዩኒት መሪ ወደዚች ተማሪ ክፍል ገብቶ የምትዘፍነው የትኛዋ እንደሆነች ጠየቀ። ያኔ «ጥፋቴ ምን ይሆን?» አለች፤ ተንቀጠቀጠች። ዩኒት መሪውም ከክፍል ጓደኞቿ ነጥሎ ወደ መምህራን ቢሮ ወሰዳት።

ቢሮ ሲደርሱ «መዝፈን ትችላለች ሲባል ሰምቻለሁና እስቲ ዝፈኚ» አላት። ፒያኖ የሚጫወቱ መምህር እያጀቧት ዘፈነች። በድምጿ የተደነቁት ሁለቱም መምህራን እንዴት እስከዛሬ ሳናውቅ በሚል ተገርመው የትምህርት ቤቱን የሙዚቃ ቡድን እንድትቀላቀል አደረጉ። የትምህርት ቤቱ የሙዚቃ ቡድን አባላት ቀድሞም ልምምድ ሲያደርጉ የቆዩና በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ሥራቸውን ሲያቀርቡ የነበሩ በመሆናቸው ለትንሽ ጊዜ ከነሱ ጋር መዋሐድ ከብዷት ነበር። ነገር ግን ተፈጥሮዋ ለሙዚቃ የተሠራ ነውና ብዙም ሳትቆይ ተዋሃደች፤ለመደች።

አመሐ ደስታ ትምህርት ቤት አርባኛ ዓመቱን ሲያከብር ከትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በተጨማሪ በርካታ የአካባቢው ነዋሪ የተሳተፉበት የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ዝግጅት ላይ የአሰፋ ደባልቄን "እንደው ክብረት ዓለም" እና የሐመልማል አባተን "የትዳሬ ማገር" የተሰኘውን ሙዚቃ በመጫወት ድንቅ ብቃቷን አሳየች። በብቃቷ የተደነቁ ተማሪዎች በርካታ ሳንቲም በመሸለማቸው የሱሪዋ ኪስ በሳንቲም ተሞልቶ ከብዶት ኖሮ ወደታች ካልወለቁ እያለ አስቸግሯትም ነበር። ያኔ በሰፈሩ ዝናዋ ሲናኝ ከትምህርት ቤት አልፎ ራሷን በትልቅ መድረክ ለማየት ማለም ጀመረች፡- የያኔዋ ታዳጊ የአሁኗ ዝነኛ ድምፃዊ ኀብስት ጥሩነህ።

የኀብስት ጥሩነህን የመድረክ ብቃት ያዩ ቤተሰቦቿ የሷ ድምፅ የተለየ መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ለዚህም ይመስላል ቤተሰቦቿ በኩራት ስለኀብስት ብቃት በየሄዱበት መናገር የጀመሩት። ታላቅ ወንድሟ ከጓደኛው ጋር በጨዋታ መሐል ታናሽ እህቱ የሚገርም ድምፅ እንዳላት ይነግረዋል። ይህን የሰማው ጓደኛው የታንጎ ሙዚቃ ቤት ባለቤት የሆነው ዓሊ አብደላ ኬፋን (ዓሊ ታንጎ) እንደሚያውቀውና እሱ ጋር ቢወስዷት ጥሩ እንደሆነ ይነግረዋል። ወንድሟ በሀሳቡ በመስማማቱ ወደ ታንጎ ሙዚቃ ቤት ያቀናሉ። ዓሊ ታንጎም ካሴት ማውጣት ከፈለገች ደፋር ዘፋኝ መሆን እንዳለባት ይናገራል።

ከእድሜዋ ትንሽነት አንጻር ዘፋኝ ትሆናለች ብለው ያላመኑት አቶ ዓሊ «እስቲ ዝፈኚ» አሉ። ያኔ በዛው በታንጎ ሙዚቃ ቤት ከወጣ ቅርብ ጊዜ የሆነውን የንዋይ ደበበን "የጥቅምት አበባን "ዘፈነች፤ የሐመልማል አባተን በድንቅ ብቃት ደገመች። ያኔ ዝፈኚ ስትባል ያለፍርሃት ሰዎች ባሉበት ዘፍናለችና "የምታድግ ልጅ ናት" ሲሉ ዓሊ ታንጎ ካሴት ሊያወጡላት ተስማሙ። እናም ከገጣሚያንና ዜማ ደራሲያን ጋር መገናኘት ጀመረች። የሙዚቃ ቤቱ ባለቤት ያኔ ብቸኛ ለነበረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚገርም ድምፅ ያላት ትንሽ ልጅ አለችና



ድምፃዊት ኀብስት ጥሩነህ

ብትመለከቷት ሲሉ ጥቆማ ሰጡ። ጥቆማውን ተቀብለው የተመለከቷት የቴሌቪዥን ጣቢያው ሰዎች በብቃቷ ስለተማመኑ የብዙነሽ በቀለን "የሚያስለቅስ ፍቅር" እያዜመች የ120 መዝናኛ ፕሮግራም ላይ ቀረበች።

አፍሮ ፀጉር ቡኒ ሹራብ የሚያሳሳ የልጅነት መልክ ይዛ የምታዜመው ታዳጊ የብዙዎች ትውስታ ናት። በ1985 ዓ.ም ከማትሪክ ፈተናዋ ተቀራራቢ ጊዜ ውስጥ «በርቺ በሉኝ» የተሰኘ የመጀመሪያ አልበሟ በታንጎ ሙዚቃ ቤት አማካኝነት ገበያ ላይ ዋለ።

**እምቡጥ ነኝ ለሚያየኝ**
**እምቡጥ ነኝ ጽጌረዳ**
**ለሁሉም አዲስ ነኝ**
**ጀማሪ ነኝ እንግዳ**
**ምኑንም የማላውቅ……**
**በርቺ በሉኝ**
**አይዞሽ በሉኝ**
**ጀማሪ ነኝና በርቺ በሉኝ**

በዚህ ዘፈን አስራ አምስት ዓመቴ ነው ብላ በመናገሯ በተለያዩ መድረኮች ላይ እድሜዋን መደበቅ የማትችል አርቲስት ይሏታል። በወቅቱ አባቷ የትምህርት ሚኒስቴር ጸሐፊና የቤተክርስቲያን አገልጋይ በመሆናቸው ከተወሰኑ ሰዎች "ልጅህ ስትዘፍን እንዴት ዝም ትላለህ?" የሚል አስተያየት ቀርቦላቸው ነበር። አባቷ ፈጣሪ የሰጣት ፀጋ ነው በማለት ለሙዚቃ ሥራዋ ድጋፍ እንደቸሯት በተለያየ ጊዜ ከሚዲያዎች ጋር በነበራት ቆይታ ገልጻለች። ያኔ እውነትም የአስራ አምስት ዓመት ታዳጊ ናትና ትኩረቷ ሥራዋ ላይ ነበር። እድሜዋ ለሙዚቃ ሥራ የደረሰ ባለመሆኑ እሷን ወክሎ የሚፈርመውም ሆነ ክፍያዎችን የሚቀበሉት አባቷ ነበሩ። ሙዚቃ ቤቱ አልበሙን ለመሥራት በሦስት ሺ ብር ክፍያ የተስማሙ ቢሆንም ስኬታማ በመሆኑ ተጨማሪ ክፍያ ተሰጥቷታል። ምንም እንኳን ከልጅነቷ የተነሳ በልኳ ባይገኝም ለቪድዮ መቀረጫ የሚሆኑ ልብስና ጌጣጌጦችንም የሙዚቃ ቤቱ ባለቤት ናቸው ያሚሉላት። በዛ ወቅት «ከእነሱ ጋር መሥራቴ ዕድለኛ ነኝ» ከምትላቸው ሮሃ ባንድ አባላት ጋር የመሥራት ዕድሉም ገጥሚታል። ከ«በርቺ በሉኝ» ሙዚቃ በተጨማሪ በየአልበሞቿ የተካተቱትን አምስት የኦሮምኛ ዘፈኖቿን ግጥምና ዜማ ከደረሱት ጋሽ አየለ ማሞ ጋር ሠርታለች።

በመጀመሪያው አልበሟ የተካተቱት እናቴን አደራ፣ ሺጋው ባንተ ላይና ምን ይሻላል የሚሉት የሙዚቃ ሥራዎቿ አሁንም ድረስ ዘመን ተሻግረው ይደመጣሉ። በዚሁ አልበም ሥራ የተካተተውና «ሺጋው ባንተ ላይ» የተሰኘው ሥራ ብቸኛው የፍቅር ዘፈን ነበርና እንዴት በዚህ እድሜዋ የፍቅር ዘፈን ትዘፍናለች ተብላ ተቃውሞ ደርሶባታል። "እናቴን አደራ" የተሰኘ ዘፈኗ ደግሞ የእናትን ፍቅር ኃያልነት ያጎላና አሁንም ድረስ በርካቶች ሲሰሙት የሚያነቡለት ተወዳጅ ሥራዋ ነው። ያኔም አሁንም ወደፊትም ዘመኑን የሚመጥን የእናትን ውለታ የልጅን ብድር ለመክፈል ያለ ጉጉት የሚተርክም ነው።

**አደራን አደራ**
**እምዬን አደራ**
**ጠብቃት አደራ**
**አምላክ አትግደለኝ**
**ቁምነገር ሳልሠራ**
**እምዬን አደራ**
**ሲታጠፍ አንጀቷ**
**እምዬን እናቴን**
**የሰው ቤት ሲደምቅ ዓውዳመቱ**
**ሲጫወት ሲስቅ ጎረቤቱ**
**ስታዝን እምዬ እየከፋት**
**መቆሚያ መሄጃ እየጠፋት**
**እንደሰው ሳትስቅ አንድ ቀን ሳይደላት**
**እባክህ ጌታዬ ሳያልፍ አትግደላት**

የኀብስት ጥሩነህ አልበም በከተማው በሚገኙ ሙዚቃ ቤቶች ተለጥፎ ዝናዋ ቢናኝም ከሙዚቃ ሥራዋ ጎን ለጎን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷ ቀጥላለች። አልበሟ ሽፋን ላይ ያለው ፎቶ በየሙዚቃ ቤቱ ደጃፍ ከመሰቀሉ በላይ በርካታ ሙዚቃዎቿ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተቀርጸው ይተላለፉ ነበር። በዚህ የተነሳም የምትማርበት ክፍል ስትገባና ስትወጣ እሷን ሊያይ የሚመጣ ተማሪ ቁጥር ቀላል አልነበረም። እሷን የሚፈልግ ተማሪ በሙብዛቱ ከተማሪዎች ዘግይታ ለመግባትና መውጣት ተገዳለች። ያኔ የመኖሪያ ጊቢያቸው አጥር የእንጨት ሆኖ በየመሐሉ ክፍተት ነበረው። ከእህቶቿ ጋር ስትጫወት ኀብስት ሲባል ሊያያት የሚፈልገው አልፎ ሂያጅ አጥራቸው ላይ ቢበረክት፤ የሰውን ትኩረት ለመቀነስ ሲባል ወላጆቿ ሐና የሚል ሌላ የቤት ስም እስከማውጣትም ደርሰዋል።

ከታንጎ ሙዚቃ ቤት ጋር ሁለተኛ አልበሟን ብትጀምርም የሙዚቃ ቤቱ ባለቤት ከሀገር ሊወጡ በማሰባቸው ከኤሌክትራ ሙዚቃ ቤት ጋር አገናኟት። የመጀመሪያውን ሁለት አልበሞች በሀገሪቱ ዝናቸው ጣራ ከነካው ሮሃ ባንድ ጋር ሠርታለች። ሦስተኛውን አልበም ከሠርጉዓለም ተገኝና ዳዊት መለሰ ጋር በመጣመር ለአድማጭ አቅርበዋል። ኤክስፕረስ ባንድ የጥምረቱ አካል ነበር። ሦስት አልበሞችን ካወጣች በኋላ ኑሯዋን አሜሪካ አደረገች። ሆኖም በርካታ የጥበብ ሰዎች ይዛ የጠፋችው አሜሪካ እሷን ልታጠፋት አልቻለችም።

ከአሜሪካ ወደ ሀገር ቤት በመመላለስ ግጥምና ዜማ በመውሰድ "ይቅርታ" አልበምን ሠራች። አሜሪካን ሆና የሠራችው "ይቅርታ" አልበምን በወቅቱ እዛው ይኖር የነበረው እውቁ አቀናባሪ አበጋዝ ክብረወርቅ አቀናብሮላታል። የአልበሙ ቅንብር በሦስት ሳምንት መጠናቀቁን ተናገራለች። ለዚህም ግጥምና ዜማውን ለማብላላት ጊዜ መውሰዷና፤ ዝግጁ ስትሆን ስቱዲዮ እንደምትገባ ገልፃለች። አምስተኛ አልበሟን "ተጣልተናል ወይ"፤ የሙዚቃ አቀናባሪው አበጋዝ ክብረወርቅ መኖሪያውን ወደኢትዮጵያ ከቀየረ ወዲህ ወደ እርሷም ኢትዮጵያ መጥታ አቀናብሮላታል።

ከአምስተኛ አልበሟ "ታገሰኝ" ለተሰኘው በሀገረ አሜሪካ ቪድዮ ክሊፕ ተሠርቶለታል። "ሲመሽ መጣ" የተሰኘው ዘፈን ለማስታወቂያ ሥራ ወደ ኢትዮጵያ በመጣችበት ወቅት የቪዲዮ ክሊፑን በቢሾፍቱ ሠርታለታለች። በተለይ በሐይቅ የተሠራው ክፍል ላይ እሷ ያለችበት አነስተኛ ጀልባ ቀዳዳ ያለውና ውሃ የሚያስገባ በመሆኑ ሌሎች ሰዎች በትልቅ ጀልባ ሆነው ውሃ በባልዲ እየተቀዳ ቀረጻው ተካሂዷል። በሰዓቱ ባልፈራም ቀረጻው ከተጠናቀቀ በኋላ እንዲህ ቢሆንስ በማለት ሊደርሱ ይችሉ የነበሩ አደጋዎችን ሳስብ ፈርቻለሁ ትላለች።

መሐሙድ አሕመድ፣ በዛወርቅ አስፋው፣ ትዕግስት አፈወርቅ እና ሌሎችም በርካታ አርቲስቶች በተካተቱበት የትዝታዎች ትዝታ ላይ "ወራሽ ያጣ ፍቅር" የተሰኘ የትዝታ ሥራዋ ተካቷል። ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ "እናምራለን"፣ "እጠብቅሀለሁ"እና "ቀረ እንዴ" የተሰኙ ነጠላ ዘፈኖችን ለአድማጭ ተመልካች ምስልን ከድምፅ አዋሕዳ አቅርባለች።

የመጀመሪያ አልበሟ መውጣትን ተከትሎ ቪድዮ ልትቀረጽበት ከሄደችበት የወቅቱ ዝነኛ የምሽት ክለብ ሁለት ነገር አትርፋለች። በድምጿ የተማረኩት የቤቱ ባለቤት በቤቱ እንድትዘፍን ሥራ ሰጧት። በሂደት የቤቱ ባለቤት ልጅ ከሆነው ባለቤቷ አቶ ግርማ ሞገስ ጋር መገናኘቷ ሌላው ትርፏ ነው። ያኔ የተጀመረው የፍቅር ጥንስስ 20 ዓመታትን ተሻግሮና በአንድ ሴት ልጅና ወንድ ልጅ ተባርኮ አሁንም በፍቅር ይኖራሉ። መኖሪያዋን በአሜሪካ አድርጋ በርካታ ሥራዎችን ለመሥራቷ አንዱ ምስጢር የባለቤቷ ድጋፍ መሆኑን ትናገራለች።

"ዘፈኖቼን ስሰማ ደስ ይለኛል" የምትለው ኀብስት በአንድ ወቅት በመሰንበቻ የሬዲዮ ፕሮግራም ላይ በነበራት ቆይታ "ኀበዝ ኀብስትዬ እያልኩ እሰማለሁ።" ብላለች። የኀብስት ተክለሰውነት ተስተካክሎ ዘመናትን ተሻግሯል። የዚህ ምስጢርም ስፖርትና የምትበላውን የምግብ አይነትና መጠን መቆጣጠር መሆኑን ትናገራለች። እናቴን አደራ፣ ሺጋው ባንተ ላይ፣ ቆይ ብቻ፣ አረ አስጥሉኝ፣ በፈጠረህ፣ ሁሉን ነገር ትቼ፣ ወፍ ሳይንጫጫ እና ተጣልተናል ወይ ከሥራዎቿ መሐል በብዙዎች የሚታወሱ ናቸው። አሁንም ቢሆን ተጨማሪ ተወዳጅና ጥዑም ዜማዎችን ለአድማጭ ጆሮ ጀባ እንደምትል ይጠበቃል!!

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የሳይበር ደኅንነት የዲጂታል ኢትዮጵያ ዋስትና ነው

5ኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደኅንነት ወር ማጠቃለያ መርሐ-ግብር "የቁልፍ መሠረተ ልማት ደኅንነት ለዲጂታል ሉዓላዊነት፤" በሚል መሪ ሃሳብ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ተካሂዷል። የሳይበር ደኅንነት ነገር ለአንድ ተቋም ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም። የሁሉንም ተቋማት ተሳትፎ ይጠይቃል። ከተሳትፎው በፊት ደግሞ በቂ ግንዛቤ ወይም የcyber security literacy መጎልበት ይጠበቅበታል። የዛሬው መጣጥፌ እዚህ ላይ ያተኩራል። ለመሆኑ የሳይበር እንዲሁም የሳይበር ደኅንነት ሲባል ምን ማለት ነው።

ሳይበር የሰው ልጅ የእርስ በርስ ግንኙነቱ ማደግ የፈጠረው ረቂቅ የቴክኖሎጂ ውጤት እና መሠረተ-ልማት፣ የመረጃ እንዲሁም የሰዎች መስተጋብር የሚገለጽበት ፈጠራ ነው። የሳይበር ምህዳር የምንለው የተለያዩ የኢንፎርሜሽን መሠረተ-ልማቶች ማለትም ኮምፒውተሮች፣ ራውተሮች፣ የኮምፒውተር ኔትዎርኮች፣ ወዘተረፈ ተሳስረው የፈጠሩት ምናባዊ ዓለም ሲሆን በዚህ ምህዳር ውስጥ ኢንፎርሜሽን ይቀመጣል፣ ይሰራጫል፣ እንዲሁም ይተነተናል። የሳይበር ምህዳሩን አንዳንዶች በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሰው ልጅ የተቆጣጠረው አምስተኛው ግዛት በማለት ይጠሩታል። ይህም ከየብስ፣ ውሃ፣ የአየር እንዲሁም የውጫዊው የኅዋ ግዛት መካከል በመመደብ።

የሳይበር ምህዳር የብዙዎቻችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ አካል ከሆነም ውሎ አድሯል። ይህ ሲባል ለሥራ፣ ለትምህርት፣ ለመዝናኛ ከመጥቀምም አልፎ ለተለያዩ የእርስ በርስ ግንኙነቶች ማሳለጫ አድርገን የምንጠቀምበት ዋነኛ መሣሪያ በመሆን ላይ ይገኛል። ከዚህ አልፎ የምህዳሩ እውን መሆን የኢንፎርሜሽን ዋጋ ከምንጊዜውም በላይ እንዲጨምር ምክንያት እየሆነ ይገኛል። የሳይበር ምህዳር የምንለው ኮምፒውተሮች ብቻ የሚፈጥሩት ሳይሆን የተለያዩ አካላት ተሳስረው እውን ያደረጉት ምህዳር ነው። እነዚህ የሳይበር ምህዳር አካላት ከላይኛው የምህዳሩ ክፍል እስከ ታችኛው ድረስ በ4 ዋና ዋና ክፍሎች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል።

የውስጠኛው የምህዳሩ ክፍል፤ የሳይበር ምህዳር እውን እንዲሆን መሠረት የጣለው አካላዊ ወይም ፊዚካል ደረጃ የምንለው ነው። ይህም የተለያዩ ማሽኖች፣ ኮምፒውተሮች፣ ኬብሎችና የመሳሰሉ አካላት ጥምረት ነው። ሁለተኛው የሳይበር ምህዳር ፤ ውስጥ የሚቀመጠው፣ የሚተነተነው እና የሚሰራጨው ኢንፎርሜሽን ነው። ሦስተኛው የሳይበር ምህዳር ክፍል ለኢንፎርሜሽን መፈጠር፣ መተንተንና መሰራጨት መሠረት የሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶች ናቸው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የኢንተርኔት አገልግሎት ፕላትፎርሞች ናቸው። የመጨረሻው እና ውጫዊ ክፍሉ፤ የሳይበር ምህዳሩን የሚጠቀመው፣ ኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂውን የሚያንቀሳቅሰው የሰው ልጅ የሳይበር ምህዳር ውጨኛው ክፍል ነው።

ከሳይበር ምህዳሩ ልዩ ባሕሪያት፤ ያልተማከለ ወይም ልዩ የተማከለ አስተዳደር የሌለው ሲሆን ይህም ለቁጥጥር አዳጋች እንዲሆን፤ ለግለሰቦች እና ለቡድኖች ከፍተኛ ኃይል የሚሰጥ ሲሆን የግለሰቦች እና ቡድኖች አስተሳሰብ፣ እምነት እና እሴቶችን ማንጸባረቅ የሚያስችል፤ የጎንዮሽ እና ትስስራዊ ኃይል የሚያበረታታ፤ ዓለም አቀፋዊ እና ድንበር የለሽ፤ እውቀት መረጃና ምናባዊነት ላይ ያተኩራል፤ ለደካሞች ልዩ ተጠቃሚነትን የሚሰጥ ነው፤ ሁሉም ጋር የመድረስ አቅም ያለው እና በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ የሆነ ፍልስፍናዊ ባሕሪያት አሉት።

በእነዚህ ልዩ ባሕሪያት ምክንያት ምህዳሩ ለተጠቃሚዎች መልካም ዕድሎችን ይዞ መጥቷል። በዚህም ምክንያት ዓለማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለየ መልክ እየያዘች ከመምጣቷ ባሻገር የእውቀት እና የኢንፎርሜሽን ማኅበረሰብ እየተፈጠረ ይገኛል። ሆኖም ግን እነዚህ መልካም ዕድሎች ካመጧቸው ትሩፋቶች ጎን ለጎን ምህዳሩ የተለያዩ የደኅንነት ስጋቶችን ይዞ መጥቷል። እነዚህን ስጋቶች ለመቋቋምና ምህዳሩ ያለውን መልካም ጎኖች አሟጦ ለመጠቀም ሃገራት የደኅንነት ስትራቴጂዎች ከቴክኖሎጂ፣ ከሰው ልጆች እንዲሁም ከኢንፎርሜሽን ደኅንነት አስተዳደር እና አሠራር ሥርዓቶች አንጻር ቀርጸው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ከስትራቴጂዎች መካከልም የኢንፎርሜሽን ደኅንነት ገዥ ሰነዶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ሳይበር የአገልግሎቱ ደኅንነት የተረጋገጠ ካልሆነ በአሉታዊ ጎኑ የሚፈጥራቸው ቀውሶች ቀላል አይደሉም። የሳይበር ጥቃት ሆን ተብሎ ያልተፈቀዱ የኮምፒውተር ሥርዓቶችን፣ መሠረተ-ልማቶች እና ኔትዎርኮች ላይ አጥፊ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም በሕገወጥ መንገድ መረጃዎችን መበዝበዝ እና አገልግሎት የማስተጓጎል ተግባር ነው። የሳይበር ጥቃቶች በአብዛኛው ሲስተሞች፣ የኮምፒውተር ሥርዓቶች እና መጠቀሚያ መሣሪያዎችን ክፍተት በመጠቀም የሚሰነዘሩ ናቸው። በማኅበራዊ የትስስር-ገፆች ላይ ደግሞ ከባሕልና ከሥነ-ምግባር ውጪ ባፈነገጠ መንገድ ከሚለጠፉ ምስሎች እና መልዕክቶች ጀምሮ የመረጃ መረብን ተገን በማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈፀሙ የመረጃ ስርቆቶች የሳይበር ጥቃት ማሳያዎች ናቸው።

በሀገራችንም ኮምፒውተርንና የኮምፒውተር መሠረተ ልማትን በመጠቀም አገልግሎትን በሚሰጡ ተቋማት ላይ አያሌ የጥቃት አደጋዎች ተደቅነዋል። በ2011 ዓ.ም ዘጠኝ ወራት ብቻ ከ488 በላይ አደገኛ የሚባሉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በሳይበር ወንጀለኞች አማካኝነት የተፈጠሩ ሲሆን በድረ-ገጾች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። ከ2004 ወዲህ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ በሃገሪቱ የሚሰነዘሩ ማንኛውንም የሳይበር ጥቃት የመመከት ኃላፊነት ወስዶ እየሠራ ይገኛል።

ተቋሙ በሀገር ደረጃ የሳይበር ደኅንነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ከማቀናጀት እና ከመምራት በላይ በየተቋማቱ የኢንፎርሜሽን ደኅንነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ ባሕል እንዲዳብር፣ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ እና አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ከፍተኛ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ኤጀንሲው ጥቃቶች ከመታሰባቸው ጀምሮ ክትትል በማድረግና ለይቶም በመተንተን ምላሽ በመስጠት ላይ ይገኛል። በቀጣይም የሳይበር ጥቃትን የመለየት፣ የመተንተንና የመመከት አቅም እየዳበረ በሄደ ቁጥር ኅብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጠረው በራስ መተማመን በዛው ልክ ይጨምራል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ እንደመጡ ያመለክታሉ። ጥቃት ፈጻሚዎቹ "በሀገር እና በዜጎች ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው" ድርጊቱን ይፈጽማሉ። ሁሉም የሳይበርም ይሁን የኔትወርክ ሰርጎ ገቦች ግን ጥፋት ፈጻሚዎች አይደሉም። በሳይበር ምህዳሩ የነጭ፣ የግራጫ እና ጥቁር ባርኔጣ የመረጃ በርባሪዎች በአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ መሠረትም ጥሩ አድራጊዎቹን "ባለ ነጭ"፣ ጉዳት አድራሾችን "ባለ ጥቁር" ከሁለቱም ውጪ የሆኑት እና መሐል ላይ የሚዋልሉትን "ባለ ግራጫ" ባርኔጣ ይሏቸዋል። የኮምፒውተሩ ዓለም ታዲያ ይህን ተምሳሌታዊነት በመውሰድ "ዋይት ሀት፣ ግሬይ ሀት እና ብላክ ሀት ሀከርስ" በሚል የኮምፒውተር በርባሪዎችን ጎራ ለመለየት ተጠቅሞበታል።

በመጀመሪያ ደረጃ ሀከር ማለት የሆነ ሰው ዕቃም፣ ኮድም ሊሆን ይችላል ከተሠራበት ዋና ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር እንዲውል ማድረግ ማለት ነው። ለምሳሌ ኋይት ሀት ሀከር ማለት፤ የሶፍትዌር ፕሮግራመሮች ወይም የአንፎርሜሽን ደኅንነት ባለሙያዎች ሆነው ሶፍትዌር፣ ሀርድዌር እና ኦፐሬቲንግ ሲስተም ላይ ያለውን ድክመት

**የሳይበር ምህዳር የብዙዎቻችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ አካል ከሆነም ውሎ አድሯል። ይህ ሲባል ለሥራ፣ ለትምህርት፣ ለመዝናኛ ከመጥቀምም አልፎ ለተለያዩ የእርስ በርስ ግንኙነቶች ማሳለጫ አድርገን የምንጠቀምበት ዋነኛ መሣሪያ በመሆን ላይ ይገኛል**

በማግኘት ለሚሠራውና ኃላፊነት ላለበት ድርጅት፣ የሚያሳውቁ ናቸው። የተፈጠረው ክፍተት ምርቱን ለሠራው ድርጅት በነፃ ወይም በክፍያ የሚሰጡ እና የሚያሳውቁ ናቸው።

የ"ኋይት ሃት ሀከርስ" ዋና ዓላማ ለሶፍትዌር አምራችም ሆነ ድርጅት፣ ለኔትወርክ ባለቤትም ሆነ ለሚገባው ሰው ችግሮችን ፈልፍሎ አውጥቶ ማሳወቅ ነው። እንደ ብላክ ሃት ሀከር የብርበራቸውን ግኝት ለመጥፎ ዓላማ አያውሉትም። የመረጃ በርባሪዎች ብዙውን ጊዜ አንድ ሶፍትዌር የተጻፈበትን ኮድ ሰብረው መግባት የሚችሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ኮዱን ሳያዩ ችግር ማግኘት የሚችሉም ናቸው።

መልካም የመረጃ በርባሪ "ኋይት ሃከር" የሆነ ኩባንያ ሙሉ ለሙሉ ፈቅዶልህ 'ክፍተታችንን አሳየን፣ ምን ድክመት አለብን?' ስትባል ቁጭ ብለህ የተለያዩ መሣሪያዎችን ወይም ችሎታህን ተጠቅመህ ክፍተቱን አግኝተህ መጠቆም ሲቻል ነው። በእርግጥ የ'ዋይት ሃት ሃኪንግ' ሲጀመርም በኢንዱስትሪው ውስጥ ክብር፣ ዕውቅና እና ዝና ከማግኘት ጋር የተያያዘ ነበር። ባለሙያዎቹ በዋነኛነት ድርጊቱን የሚያከናውኑት ለሙያው ፍቅር ሲሉ እንደነበር ፍጹም ይገልጻል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሊዮን ዶላር የሚያንቀሳቅሱ የቴክኖሎጂ ድርጅቶች ችግሮቻቸውን ነቅሰው ለሚያወጡላቸው ለ'ዋይት ሀት ሀከሮች' ዕውቅና ከመስጠት ተሻግረው ዳጎስ ያለ ክፍያም እንደማበረታቻ መስጠት ጀምረዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃም ይሁን እንደ ዓለም የሚደረጉ የሳይበር ጥቃቶች፤ በተለይም በመሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈጸሙ የሳይበር ጥቃቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል። ሳይበር በባሕሪው ድንበር የለሽ፣ ውስብስብ እና ኢ-ተገማች በመሆኑ አንድ ሀገር የሳይበር ደኅንነት አቅሙን ካላሳደገ ሀገራዊ ሉዓላዊነቱ እና ብሔራዊ ጥቅሙ ከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቃል ይለናል የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያ የሳይበር ምህዳሩን የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር መጨመርን ተከትሎ በግለሰቦችና ተቋማት ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶችን ጨምሮ በሀገራችን ቁልፍ የመንግሥት መሠረተ-ልማቶች ላይ እየደረሱ ያሉ የጥቃት ሙከራዎች የብሔራዊ ደኅንነት ስጋት መፍጠራቸው አልቀረም።

በኢትዮጵያ ከሚፈጸመው የሳይበር ጥቃት 90 በመቶው በግንዛቤ ጉድለት የሚያጋጥም ነው። በኢትዮጵያ በ2015 ዓ/ም 6 ሺ 959 የሳይበር ጥቶች መፈጸማቸው፤ ከእነዚህ ውስጥ 2 ሺ 559 ያህሉ በድረ ገጽ ላይ የተፈጸሙ ሲሆኑ፤ 1 ሺህ 295 ደግሞ የማልዌርና የፒሺግ መሆናቸው ተጠቁሟል። እንዲሁም 603 በመሠረተ ልማት ቅኝት፣ 1 ሺህ 493 መሠረተ ልማት የማቋረጥ (አብዛኛው የፋይናንስ ተቋማትን ዒላማ ያደረገ)፣ 695 ሰርጎ የመግባት ሙከራ እና 145 ሌሎች የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተደርገዋል። የሳይበር ጥቃቶቹ የፋይናንስ እና የፀጥታ ተቋማትን፣ እንደ ቴሌኮምና መብራት ያሉ ቁልፍ ተቋማት መሠረተ ልማቶችንና ቁልፍ የመንግሥት ተቋማትን ዒላማ ያደረጉ ነበሩ።

የተሰነዘሩ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችን መከላከል በመቻሉም በሀገር ላይ ሊደርስ የነበረ 23.2 ቢሊዮን ብር ኪሳራ ማዳን መቻሉን መገለጹ አይረሳም። ለመሆኑ ኢንፎርሜሽን ወይም መረጃና የሳይበር ደኅንነት ያላቸው ትስስር ምንድን ነው? ኢንፎርሜሽን ለአንድ ሀገር ሠላም፣ ልማት፣ ዲሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር ግንባታ መሳካት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት እሙን ነው። በተለይም አሁን በምንገኝበት የኢንፎርሜሽን ዘመን የአንድ ሀገር የኃያልነትና የልዕልና ውጤት ምስጢርም ይኸው ኢንፎርሜሽን መሆኑ እርግጥ ነው። ታዲያ ይህ ኢንፎርሜሽን ደኅንነቱ ተጠብቆና ተረጋግጦ ለሚፈለገው ዓላማ ካልዋለ እና በተቃራኒው ለእኩይ ዓላማ የሚውል ከሆነ የሚያስከትለው ጉዳት እጅግ የከፋ ነው የሚሆነው።

የኢንፎርሜሽን ደኅንነት ስንል የኢንፎርሜሽኑን ታማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኢንፎርሜሽኑ ባልተፈቀደለት ሰው/አካል እንዳይቀየር፣ ከነበረው የተለየ ቅርፅ እንዳይዝ፣ እንዳይሰረዝ እና እንዳይደለዝ ምልዑነቱን የማረጋገጥ እና ኢንፎርሜሽኑ በተፈለገው ሰዓት እና ጊዜ ኃላፊነቱ ላለው እና ለተፈቀደለት አካል ያለምንም እክል ተደራሽ የማድረግ ሂደት ነው።

ይህም ማለት የኢንፎርሜሽኑን ምስጢራዊነት፣ ተደራሽነት እና ምልዑነት ማረጋገጥ ማለት ነው። ከዚህ አኳያ የኢንፎርሜሽን ደኅንነትን የማረጋገጥ ጉዳይ የሦስት ነገሮች መስተጋብር ውጤት መሆኑን የኢንፎርሜሽን ደኅንነት ባለሙያዎች ያትታሉ፤ እነዚህም ቴክኖሎጂያዊ የመከላከያ መንገዶች፣ የተለያዩ አሠራሮች፣ ሕጎች እና ሥርዓቶች እንዲሁም የሰው ልጅ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የሰው ልጅ ዋነኛው የኢንፎርሜሽን ቋትና የደኅንነት ስጋት የተጋላጭነት ምንጭ እንደሆነ ብዙዎቹ ይስማሙበታል።

# ዓለም አቀፍ

## በትራምፕ የግድያ ሙከራ ሴራ ላይ ተሳታፊ ነበር የተባለው አፍጋኒስታናዊ ተከሰሰ

የአሜሪካ መንግሥት ዶናልድ ትራምፕ ቀጣዩ ፕሬዚዳንት ሆነው ከመመረጣቸው በፊት ኢራን ለመግደል አሲራለች ካለው ጋር በተያያዘ ተሳታፊ ተብሎ የተጠረጠረ አፍጋኒስታናዊ ላይ ክስ መሠረተ። የፍትህ ሚኒስቴር ትራምፕን ለመግደል "እቅድ የማቅረብ" ኃላፊነት ተሰጥቶት ተሳትፏል ሲል በወነጀለው የ51 ዓመቱ ፋርሃድ ሻኬሪ ላይ የመሠረተውን ክስ ይፋ አድርጓል።

የአሜሪካ መንግሥት ሻኬሪ በቁጥጥር ስር አለመዋሉን ገልጾ፣ ኢራን ውስጥ ይኖራል ተብሎ እንደሚታመን ገልጿል። በማንሃተን ፍርድ ቤት በቀረበው በዚህ የወንጀል ክስ፣ አቃቤ ሕግ በኢራን የአብዮታዊ ጥበቃ ባለሥልጣን የሆነ ግለሰብ ሻኬሪ ትራምፕን እንዲሰልል እና የግድያ ዕቅድ እንዲያቀርብ በመስከረም ወር ላይ መመሪያ መስጠቱ ተብራርቷል።

የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የሆኑት ሜሪክ ጋርላንድ በሰጡት መግለጫ "የፍትህ መሥርያ ቤቱ የኢራንን መንግሥት አካል ላይ ክስ የመሠረተው፣ አስተዳደሩ የወንጀል ተባባሪዎችን የኢራንን የግድያ ሴራ በዒላማዎቹ ላይ፣ተመራጩ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕን ጨምሮ እንዲፈጽሙ በመታዘዛቸው ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

የፍትህ መሥርያ ቤቱ ኢራንን በመተቸት የሚታወቅ አሜሪካዊ ጋዜጠኛን ለመግደል ተመልምለዋል ያላቸውን ሁለት ሌሎች ግለሰቦችም ላይ ክስ መሥርቷል። በፍትህ መሥርያ ቤቱ ክስ የተመሠረተባቸው ሌሎቹ ግለሰቦች ካርሊስሌ ሪቬራ በመባል የሚታወቀው የ49 ዓመት ጎልማሳ ከብሩክሊን እና የ36 ዓመቱ ጆናቶን ሎድሆልት ከስታተን አይላንድ እንደሆኑ አብራርቷል።

ሁለቱ በኒውዮርክ በሚገኝ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በእስር ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል። ትራምፕ በዚህ ዓመት ሁለት የተለያዩ የግድያ ሙከራዎች አጋጥሟቸዋል። በሐምሌ ወር ላይ አንድ ታጣቂ የቀድሞ ፕሬዚዳንቱ በፔንስልቬንያ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ እያሉ



ተኩሶባቸው ጆሯቸውን ጨርፏቸዋል።

በመስከረም ወር እንዲሁ ሌላ ግለሰብ ትራምፕ በዌስት ፓልም ቢች በሚገኝ መኖርያ ቤታቸው ጎልፍ ሲጫወቱ ጦር መሣርያ በማነጣጠሩ በቁጥጥር ስር ውሏል። አፍጋኒስታናዊው ሻኬሪ ትራምፕን በሰባት ቀናት ውስጥ የመግደል እቅድ እንዲያወጣ ተጠይቆ ነበር ሲል ያትታል በአሜሪካ አቃቤ ሕግ የቀረበው ክስ።

እንደ አቃቤ ሕግ ገለጻ፣ ሻኬሪ ትራምፕን ለመግደል በሰባት ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሃሳብ ማቅረብ ባለመቻሉ፣ የኢራን አብዮታዊ ጥበቃ ባለሥልጣናት እቅዱን ለጊዜው ገትተውታል።አቃቤ ሕግ ሻኬሪን ጠቅሶ እንዳለው የኢራን መንግሥት ዶናልድ ትራምፕ በምርጫው ይሸነፋሉ ብሎ በማመኑ ከምርጫው በኋላ ለመግደል መሞከር ቀላል እንደሚሆን መወሰናቸውን ገልጿል።

አቃቤ ሕግ ሻኬሪን በልጅነቱ ወደ አሜሪካ የመጣ አፍጋኒስታናዊ ዜግነት ያለው ሲል ገልጾታል። በአውሮፓውያኖቹ 2008 ለ 14 ዓመታት ከስርቆት ወንጀል ጋር በተያያዘ በእስር ካሳለፈ በኋላ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ተደርጓል። አቃብያነ ሕጎች እንዳሉት የ51 ዓመቱ ጎልማሳ፣ የኢራን መንግሥት ዒላማ የሆኑ ግለሰቦች ላይ ክትትል ለማድረግ በእስር ቤት የሚገኙ "የወንጀል ተባባሪዎች መረብ"ን ሪቬራ እና ሎድሆልትን የሚባሉ ግለሰቦችን ጨምሮ ተጠቅሟል።

ሻኬሪ ለሪቬራ እና ሎድሆልት የኢራንን መንግሥት የሠብዓዊ መብት ረገጣ እና ሙስና የዘገበውን አሜሪካዊውን ጋዜጠኛ ለመግደል 100 ሺህ ዶላር ቃል ለመክፈል ቃል ገብቷል ሲል አቃቤ ሕግ በክሱ ላይ አመልክቷል። ስሙ ያልተጠቀሰው ጋዜጠኛ ከዚህ ቀደምም ዒላማ ተደርጎ ነበር ሲል አቃቤ ሕግ ተናግሯል።

አርብ ዕለት በማህበራዊ ሚዲያ ላይ መቀመጫዋን ብሩክሊን ያደረገች ማሲህ አሊነጃድ የተባለች ጋዜጠኛ ኤፍቢአይ እርሷን ለመግደል ያሴሩ ሁለት ሰዎችን ማሰሩን ጽፋለች። ገዳዮቹ ብሩክሊን በሚገኘው ቤቷ ፊት ለፊት እንደመጡ ተናግራለች። አሊነጃድ "ወደ አሜሪካ የመጣሁት በሕግ ላይ በግልጽ የተቀመጠውን የመናገር ነፃነቴን ለመጠቀም ነው፤ መሞት አልፈልግም" ስትል ጽፋለች። በተጨማሪም "አምባገነንነትን መዋጋት እፈልጋለሁ፤ እናም ደህንነቴ ሊጠበቅ ይገባል" ብላለች።

ከአሜሪካዊው ጋዜጠኛ እና ትራምፕ በተጨማሪ የኢራን መንግሥት በማህበራዊ ሚድያ ላይ እስራኤልን የሚደግፉ እና ኑሯቸውን በኒውዮርክ ከተማ ያደረጉ ሁለት የአይሁድ ዝርያ ያላቸው አሜሪካውያን ነጋዴዎችን ለመግደል ማቀዱን ክሱ ያስረዳል። ሻኬሪ ለአቃቤ ሕግ ሐማስ በእስራኤል ላይ ጥቃት ካደረሰ ከአንድ ዓመት በኋላ በጥቅምት 2024 በስሪላንካ የእስራኤል ቱሪስቶች ላይ በጅምላ ጥቃት ለማድረስ እንዲያቅድ የኢራን አካላት እንደጠየቁት ተናግሯል።

ሻኬሪ፣ ሪቬራ እና ሎድሆልት ሁሉም የተከሰሱት ግድያ ለመፈጸም በመመልመላቸው ሲሆን ይህም የ10 ዓመት እስራት ያስቀጣቸዋል። በተጨማሪም እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራት ሊያስቀጣ በሚችለው ገንዘብ ለመሰወር በማሴር እንዲሁም ለግድያ ተግባር በሦስተኛ ወገን ተመልምለው በማሴር ወንጀሎችም የሚቀጡ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





# አስገራሚው የእግር ኳስ 31 ለ 0 ውጤት!!

**ቦጋለ አበበ**

በኢንተርናሽናል የብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎች ታሪክ በርካታ ፍልሚያዎች በሰፊ የግብ ልዩነት ሲጠናቀቁ ታይተዋል። በትልቁ ዓለም ዋንጫ መድረክ ሳይቀር በሰፊ የግብ ልዩነቶች የተጠናቀቁ በርካታ ጨዋታዎች በታሪክ ተመዝግበው ይገኛሉ።

በአጠቃላይ በእግር ኳስ ታሪክ በሰፊ የግብ ልዩነት የተጠናቀቁ በርካታ ጨዋታዎች ቢኖሩም በብሔራዊ ቡድኖች መካከል በተካሄዱ ጨዋታዎችን በተመለከተ በሰፊ የግብ ልዩነት የተጠናቀቁ ብሎ ፊፋ ከመዘገባቸው ውጤቶች መካከል ዋነኛ የሆነው ከ24 ዓመት ነበር የተመዘገበው።

እግር ኳስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘመነ በዓለም ላይ የተፎካካሪ ቡድኖች ደረጃ ጎልቶ በማይታይበት በዚህ ዘመን ከደርዘን በላይ ግቦች በአንድ ጨዋታ ሲመዘገቡ ማየት ከባድ ነው፡፡ በክለብም ይሁን በብሔራዊ ቡድኖች ደረጃ እግር ኳስ ከልምድ ወጥቶ በሳይንስ እየተመራ ከመጣ ወዲህ የአሠልጣኞች የታክቲክ ብስለት እየተቀራረበ መምጣቱን ተከትሎ በጣት የሚቆጠሩ ግቦችን ብቻ በአንድ ጨዋታ መመልከት የተለመደ ነው፡፡ የአሠልጣኞች፣ ቡድኖችና የተጫዋቾች ደረጃ ፍፁም የተራራቀ በሆነባቸው ፍልሚያዎች እንኳን አንድ ቡድን ብቻ ከደርዘን በላይ ግቦችን ሲያስቆጥር ማየት እየቀረ መጥቷል፡፡ አንድ ብሔራዊ ቡድን በአንድ ጨዋታ ላይ ከ30 በላይ ግብ አስቆጥሮ ያሸነፈበት አጋጣሚ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት የተፈጠረ መሆኑ ግርምት ይፈጥራል፡፡




ይህ ታሪካዊ ጨዋታ በአውስትራሊያ 31 ለ 0 ድል የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ከባዱ ሽንፈት የደረሰባት ደግሞ በእግር ኳስ ስሟ ሲጠራ የማትታወቀው የኦሽኒያዋ አሜሪካን ሳሞአ ናት። ጨዋታው የኦሽኒያ ሀገራት የ2002 የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ነበር። በመጀመሪያ የማጣሪያ ጨዋታዋን ቶንጋን 22 ለ 0 ያሸነፈችው አውስትራሊያ፣ በፊጂ 13 ለ 0 የተሸነፈችው ሳሞአ ጋር በኮፍስ ሀርበር ስቴድየም ተገናኘች።

በሦስት ሺ ተመልካቾች ፊት የተካሄደው የአውስትራሊያና ሳሞአ ጨዋታ ገና ከአስረኛው ደቂቃ ጀምሮ ግብ ቢያስተናግድም ታሪክ የማይረሳው ውጤት ይመዘገብበታል ብሎ ያሰበ አልነበረም። የአውስትራሊያው አማካኝ ኮን ቦትሲያኒስ ሀገሩን ገና በጊዜ መሪ አደረገ። ኋላ ላይም በ50ኛው እና 84ኛው ደቂቃ ላይ ባስቆጠራቸው ግቦች ሐትሪክ ሠርቷል።

ታሪካዊ ውጤት በተመዘገበበት ጨዋታ ግን ቀዳሚዋን ግብ ከመረብ አሳርፎ ሶስታ ከሠራው ተጫዋች በላይ አርቺ ቶምሰን የተባለውና ሌሎችም የአውስትራሊያ ተጫዋቾች የጨዋታው ኮከብ ነበሩ። ቶምሰን የተባለው ተጫዋች ለማመን በሚከብድ ሁኔታ (12', 23', 27', 29', 33', 37', 42', 45', 56', 60', 65', 85', 88') ደቂቃዎች በጨዋታው አስራ ሦስት ግቦችን በተጋጣሚ መረብ ላይ በማዝነብ ታሪክ ሠርቷል።

የአጥቂ መስመር ተጫዋቹ ዴቪድ ዝሪሊችም ብዙ አልራቀም፣ (13', 21', 25', 33', 58', 66', 78', 89') ደቂቃዎች ስምንት ግቦችን ከመረብ አዋህዷል። ሌሎቹን የአውስትራሊያ ግቦች ኦሬሊዮ ቪድማር በ (14', 80') ደቂቃ፣ ቶኒ ፖፖቪች (17', 19') ደቂቃዎች፣ ሳይመን ኮሎሲሞ (51', 81') እና ፋስቶ ደ ኤሚሲስ በ55ኛ ደቂቃ ማስቆጠር ችለዋል።

ይህ የአውስትራሊያ የ31 ለ 0 ድል በብሔራዊ ቡድኖች ኢንተርናሽናል ጨዋታ ክብረወሰን ሆኖ ከ24 ዓመት በፊት ቢመዘገብም፣ በአጠቃላይ የእግር ኳስ ታሪክ አፈታሪክ ከሚመስለው የ 149 ለ 0 ውጤት ጋር ሲነፃፀር በብዙ ርቆ ይገኛል።

ብዙዎች የማያምኑት የ 149 ለ 0 ውጤት በእግር ኳስ ታሪክ ትልቁ ተብሎ ይታወቃል። ይህ ውጤት የተመዘገበውም በአፍሪካዊቷ ደሴት 2002 ላይ በማዳጋስካር ሊግ AS Adema የተሸኘ ክለብ S.O. l'Emyrne የተባለውን ክለብ የረታበት መሆኑ በብዙ የመረጃ ምንጮች ተጠቅሶ ይገኛል።